አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ | 84ኛ ዓመት ቁጥር 091 ታኅሣሥ 1 ቀን 2017 ዓ.ም | ብዕራችን ስኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

“በቀጣይ ጥቃት አድርሶ እንደተፈለገ መኖር የማይቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል”

- ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ
የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር

መክሲት ወንድወሰን

አዲስ አበባ፡- በቀጣይ ጥቃት አድርሶ እንደተፈለገ መኖር የማይቻልበት ሁኔታ እንደሚፈጠር የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ አስታወቁ፡፡ ጥቃት አድራሾችን መመዝገብ የሚያስችል ዲጂታል የመረጃ ሥርዓት እየጎለበተ እንደሆነም ጠቆሙ።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ፤ በተለይ ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፤ የሴቶችና የሕፃናት ጥቃት ከእለት ተእለት እጨመረ መጥቷል። ችግሩን ውጤታማ በሆነ መንገድ መከላከል የሚያስችል አስተማሪ ሕግ እየተረቀቀ ነው ብለዋል ።

በአሁኑ ሰአት ቀደም ሲል የነበረውን ሕግ ለማሻሻል፤ ሕጉን የመፈተሽ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ተናግረው፤ ማሻሻያው በቀደመው ሕግ ላይ የነበሩብትን ክፍተቶች በመለየት የመከላከሉን ሥራ ውጤታማ ማድረግ የሚያስችሉ ተጨማሪ ጠንካራ ሕጎች እና አሠራሮች ተግባራዊ እንደሚሆኑ አስታውቀዋል፡፡

የሕጉ መሻሻል ያስፈለገው በሴቶችና በሕፃናት ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች እየጨመሩ መምጣታቸው ፣ጥቃቶቹ በምስክር ፊት የሚደረጉ አለመሆናቸው፣ ከዛም ባለፈ ጥቃቶች እየረቀቁ በመምጣታቸው እንደሆነ አስታውቀዋል። ችግሩ በፍርድ ሂደቱ ላይ ፈተና እየሆነ መምጣቱን አመልክተዋል።

ችግሩን በተወሰነ መልኩ ለመቅረፍ፤ከሕግ ማሻሻያ ሥራው

"በቀጣይ ጥቃት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ፎቶ፡- በአዮብ ተፈሪ



የአቪዬሽን ዘርፉን በማሳደግ አዳዲስ ዕድሎችን መክፈትና ሥራ መፍጠር ይገባል

- ባለሥልጣኑ የተመሠረተበት 80ኛ ዓመት በዓል እየተከበረ ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የአቪዬሽን ዘርፉን በማሳደግ አዳዲስ እድሎችን መክፈት፣ ሥራ መፍጠር እና የአፍሪካን ኢኮኖሚ ማጠናከር እንደሚገባ ተገለጸ።

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የተመሰረተበትና የዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ማቋቋሚያ ስምምነት የተፈረመበት 80ኛ ዓመት በዓል በተለያዩ ሁነቶች በአዲስ አበባ ስካይላይት ሆቴል ከትናንት ጀምሮ እየተከበረ ይገኛል።

የትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስትር ዓለሙ ስሜ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት የአየር ትራንስፖርት የኢኮኖሚ እድገት ቁልፍ መሪ እንደሆነ ይገነዘባል። የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣንም ለአየር መንገዱ ማስፋፊያ አስፈላጊውን የቁጥጥር ድጋፍ በማድረግ የዕድገት መሰረት ሆኖ ቆይቷል።

የአቪዬሽን ዘርፉ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ለወሎ ተርሸሪ ሆስፒታል ግንባታ የተሰበሰበው 23 ነጥብ 7 ሚሊዮን ብር ባንክ አለመግባቱ ተገለጸ

- ከ9 ሚሊዮን ብር በላይ አላግባብ ወጪ መደረጉ ተጠቆመ
- ቦርዱ በሌለው ስልጣን አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ትኬቶችን የጠፉ በሚል መሠረዙም ተመለከተ

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- ለወሎ ተርሸሪ ኬር የሕክምናና ማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ የተሰበሰበው 23 ነጥብ 7 ሚሊዮን ብር ወደ ባንክ አለመግባቱን ዋናው ኦዲተር አስታወቀ። የግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ከ2010 እስከ 2016 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ድረስ ሕጋዊ እውቅና ሳይኖረው ያለ አግባብ ዘጠኝ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ብር በሥራ ማስኬጃ ስም ማውጣቱን አመለከተ፡፡

ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የ2015/16 በጀት ዓመት በወሎ ተርሸሪ ኬር የሕክምናና ማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ከህብረተሰቡ የተሰበሰበው ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ ትናንት በክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ላይ ምክክር አካሂዷል፡፡

ቋሚ ኮሚቴው ለሆስፒታሉ ግንባታ ከሕዝብ የተሰበሰበው ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ ስላለመዋሉ፣ ጽህፈት ቤቱ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ሀብቱን ኦዲት አስደርጎ ለዩኒቨርሲቲው ለምን እንዳላስረከበ፣ ጽህፈት ቤቱ የሚያከናውናቸው ተግባራት ሕጋዊነት፣ የግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ለምን በድጋሚ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅትነት መመዝገብ እንዳልቻለና ሌሎችንም ጥያቄዎች አቅርቧል፡፡

የወሎ ተርሸሪ ኬር የሕክምናና ማስተማሪያ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት እንዲሁም ሥራ አመራር ቦርድ አመራሮች በሰጡት ምላሽ፤ የሆስፒታሉን ግንባታ እውን ለማድረግ በበጎ ፈቃደኝነት ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ መቆየታቸውን ገልጸዋል፡፡

ለግንባታው ከአማራ ክልል አልፎ በመላው ኢትዮጵያ ብሎም በተለያዩ ሀገራት በሚገኙ ኤምባሲዎች ጭምር የብር ኩፖኖችንና የቶምቦላ ትኬቶችን ለመሸጥ ጥረት ተደርጓል፡፡ በአሁኑ ወቅትም ከሕዝቡ የተሰበሰበ 93 ሚሊዮን ብር በባንክ ይገኛል፡፡ከዚህ ውስጥ የተወሰኑ ትኬቶችን መሰብሰብ እንዳልተቻለ ይሁን እንጂ ከአሠራር ውጪ የተከናወነ ምንም ሥራ አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

ጽህፈት ቤቱ ለወሎ ዩኒቨርሲቲ አስረክቦ እንዲወጣ በመወሰኑ በድጋሚ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅትነት መመዝገብ እንዳልፈለጉ አስታውቀዋል፤ ዩኒቨርሲቲው እስካሁን ድረስ ስራውን ሊረከብ አልቻለም፡፡ አሁንም በተቻለ ፍጥነት ያለውን ሀብት አስረክቦ ለመውጣት

ስወሎ ተርሸሪ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

የፀረ ጾታዊ ጥቃት ንቅናቄ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተገለጸ

ሰላማዊት ውቤ

አዲስ አበባ ፡- ጥቃቶችን የማስቆምና የመከላከል ሥራና ትግል ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ እታገኘሁ አሰፋ አስታወቁ፡፡

ወይዘሮ እታገኘሁ በተለይ ለአዲስ ዘመን እንደስታወቁት፤ እንደ ሀገር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣውን ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት መከላከል የሚያስችል “ፀረ- ጾታዊ ጥቃት ንቅናቄ ዘመቻ” በሀገሪቱ ሁሉም አካባቢዎች በተለያየ መልኩ ሲካሄዱ ቆይተዋል።

ዓለም አቀፉ የፀረ- ጾታዊ ጥቃት ንቅናቄ ዘመቻ በኢትዮጵያም በሴቶች ላይ የሚደርሰውን አካላዊ፤ ስነልቦናዊ፣ ወሲባዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቃት በመቃወም ለዓመታት ሲካሄድ መቆየቱን አመልክተዋል፡፡

እነዚህን ቀናት በኅብረት በማሰብ በሴቶች ላይ ችግር እያደረሰ ያለውን ጾታዊ ጥቃት ለመግታት ሀገራዊ አጀንዳ ማድረግ በማስፈለጉ ፣ የፀረ- ጾታዊ ጥቃት የንቅናቄ ዘመቻ በኢትዮጵያ መጀመሩንም አስታውሰዋል፡፡

ከ2006 ዓ.ም ጀምሮም 18 የተለያየ አደረጃጀት ያላቸው አባላት በማሰባሰብ ጥቃቱን እየተቃወመ በሚገኘው በኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት ስር ባለው “ዘመቻ በጾታዊ ጥቃት በኢትዮጵያ ቡድን” አማካኝነት በሀገር አቀፍ ደረጃ ጥቃቱን ለመቀነስ ብሎም ለማስቆም የሚያስችሉ የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን በጋራ ሲካሄድ መቆየቱን ገልፀዋል፡፡

ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መምጣቱን መረጃዎች ማሳየታቸውን የጠቆሙት ኃላፊዋ፤ ዘንድሮም 16ቱ ብርቱካናማ ቀናት “ስለ ሴቶች ጥቃት ዝም አንልም” በሚል መሪ ቃል እንደ ሀገር በተለይም በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ለይቶ ጋዜጣዊ መግለጫ ከመስጠት ባሻገር የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ መርሀ ግብሮች ሲካሄድ መቆየቱን አመልክተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት ስር ባለው “ዘመቻ በጾታዊ ጥቃት በኢትዮጵያ ቡድን” እንዲሁም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማትና ድርጅቶች የግፊት ሥራዎችን ለመሥራት የሚያስችሉ የምክክርና የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት፤ጥቃቱ የደረሰባቸውን ወገኖች ለማሰብ የሚረዱ የሻማ ማብራት ስነስርዓቶች በማካሄድና ሌሎች ተግባራትን በማከናወን ጥቃትን በመቀነስና በማስቆም ተጨባጭ ለውጥ በሚያመጣ ሁኔታ ሲከበር መቆየቱን አብራርተዋል፡፡

“ጾታዊ ጥቃትን ለማስቀረት ተቀናጅቶ መስራት አስፈላጊ ነው” ያሉት ኃላፊዋ፤ በጋራ መስራቱ እርስ በእርስ የልምድ ልውውጥ ለማድረግ፤ እንዲሁም ዕለቱን አስመልክቶ በሚዘጋጁ የውይይት መድረኮች የተገኙ ሀሳቦችን በማደራጀት የጥቃት ሰለባ የሆኑ ሴቶቹ ለደረሰባቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጫና መንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት የበለጠ ትኩረት እንዲሰጡት ማድረግ ያስችላልም ብለዋል፡፡

በሴቶች ላይ የሚፈጸመውን ጥቃት ለማስቆም ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል የበኩሉን መወጣት እንዳለበት፤ በተለይም የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች በሴቶች ላይ እየደረሰ ያለውን ጥቃት አስመልክተው ተከታታይነት ያላቸው ስራዎች መስራት እንደሚገባቸው አሳስበዋል።

ጥቃቱን ለመቃወምና ለመከላከል ሲካሄድ የነበረው የ16ቱ ቀናት የንቅናቄ ዘመቻ ቢጠናቀቅም፤ጥቃት የማስቆም ስራና የተቃውሞ ትግሉ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ ከህዳር 16 / 2017 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ዝግጅቶች ሲካሄድ የቆየው የፀረ ጾታዊ ጥቃት ንቅናቄ ዘመቻ ትናንት ተጠናቋል።16ቱ የፀረ- ጾታዊ ጥቃት ንቅናቄ ቀን በወቅቱ ትሩጅሎ ተብሎ የሚጠራውን አምባ ገነናዊ ስርዓት ለመቃወም ሲፋለሙ በግፍ ለተገደሉ ለሦስት እህትማማቾች መታሰቢያነት እ.ኤ.አ በኖቨምበር 25 ቀን 1981 በላቲን አሜሪካዊቷ ኢንኩዊንትሮ መጀመሩ ይታወሳል።

«በሀገር አቀፍ የብክለት መግቻ ንቅናቄ የተገኙ ስኬቶችን ቀጣይ ለማድረግ እንሰራለን»

- ክልሎች

ታምሬት ተስፋዬ

አዲስ አበባ፡- በሀገር አቀፍ ደረጃ «ብክለት ይብቃ ውበት ይንቃ» በሚል መሪ ሃሳብ በተካሄደው የብክለት መግቻ ንቅናቄ የተገኙ ስኬቶችን ቀጣይ ለማድረግ እየሰሩ መሆናቸውን የኦሮሚያና የአማራ ክልሎች አስታወቁ፡፡

የኦሮሚያ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የአካባቢ ዘርፍ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ዳይሬክተር አቶ ስንታየሁ በፈቃዱ እንደሚገልጹት፤ ሀገር አቀፍ የብክለት መግቻ ንቅናቄው ዋነኛ ዓላማ የዜጎችን በጤናማ አካባቢ የመኖር ሕገ መንግሥታዊ መብት ማስከበር፣ ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ ነው። እንዲሁም ኅብረተሰቡ ስለ አካባቢ ጥበቃ፣ ብክለትና ብክነት ምንነት፣ የመከላከያና የማስወገጃ መንገዶች ላይ ግንዛቤውን እንዲያጎለብት ማድረግ ነው።

በንቅናቄው በየወሩ የፐላስቲክ፣ የአየር፣ የውሃ፣ የአፈርና የድምፅ ብክለት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የተለያዩ ተግባራት መከናወናቸውን ያመላከቱት አቶ ስንታየሁ፤ በኦሮሚያ ክልል ማኅበረሰቡን ጨምሮ የተለያዩ ተቋማትንና ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ በሁሉም ዞኖች ከተሞች እስከ ታችኛው አስተዳደር እርከን ድረስ በተናበበ ሁኔታ ተግባራዊ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

ሰፊ የግንዛቤ መፍጠሪያ ንቅናቄ መድረኮች በማዘጋጀት ከሰባት ሚሊዮን በላይ ዜጎችን መድረስ መቻሉንና ተቋማት የአካባቢ ሕግን ተከትለው እንዲሰሩ በማድረግ ረገድ በተከናወኑ የክትትልና ቁጥጥር ሥራዎች በተለይ ደረጃን ያላሟሉ ተቋማት ላይ ከመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ እስከ እገዳ የደረሱ የሕግ ማስከበር እርምጃዎች መወሰዳቸውን አብራርተዋል፡፡

አቶ ስንታየሁ በፈቃዱ

አቶ በልስቲ ፈጠነ

በክልል ደረጃ በተከናወኑ የብክለት መግቻ እንቅስቃሴዎች በሁሉ ረገድ ዘርፈ ብዙ ውጤቶችን መመልከት መቻሉን ያስገነዘቡት አቶ ስንታየሁ፤ የክልሉ ሕዝብ ስለ አካባቢ ጥበቃ ብሎም ብክለት አወጋገድ ከወትሮው በተሻለ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረውና መብቱን የሚጠይቅ ማህበረሰብ መፍጠር ተችላል። «የአካባቢ ብክለት ሲከሰትም «ብክለትን ፈጥኖ ሪፖርት የማድረግ ልምዶች ተፈጥረዋል»ብለዋል፡፡

ከሕዝብ ባሻገር የዘርፉ ተዋናዮች ላይም ከፍተኛ ለውጥ መታየት መጀመሩን ያስገነዘቡት አቶ ስንታየሁ፤ ለአብነትም በተለያዩ ዘርፎች የተሰማሩ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እንዲሁም ባለሀብቶች ከዚህ ቀደም ከነበረው በተሻለ መልኩ ለአካባቢ ደህንነትና ጥበቃ ልዩ ትኩረት መስጠት መጀመራቸውን ጠቁመዋል፡፡

«ይህ ማለት ግን ብክለትን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ በሚፈለገው ልክ ይደርሳል ማለት አይደለም፤ አካባቢ ብክለት በአንድ ሰሞንና ጊዜ ተግባር ብቻ የሚስተካከል አይደለም። ቀጣይነት ያለውን ሥራ፣ ቁርጠኝነትና ተሳትፎን የግድ ይላል። ስለዚህም የስድስት ወሩ ንቅናቄ በዚሁ ከፍታው ልክ በዚህም ዓመት እንዲቀጥል እየሠራን ነው» ብለዋል፡፡

የአማራ ክልል የአካባቢና ደን ጥበቃ ባለስልጣን ምክትል ኃላፊ አቶ በልስቲ ፈጠነ በበኩላቸው፤ «በሀገር ሀገር ብክለት መግቻ ንቅናቄ ትግበራና ውጤት ብዙ ተምረንበታል፤ በተለይም ከተሠራ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል አይተንበታል» ብለዋል፡፡ የክልሉም በብክለት መግቻ ንቅናቄው የታየው ሁለንተናዊ ተነሳሽነትና ውጤት ይበልጥ መቀጠል አለበት የሚል አቋም መያዙንና ንቅናቄው በዚህ ዓመትም ይበልጥ ቀጣይ እንዲሆን እቅድ ወጥቶለት ወደ ሥራ መገባቱን አስታውቀዋል፡፡

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አስተባባሪነትን «ብክለት ይብቃ ውበት ይንቃ» በሚል መሪ ሃሳብ ከሚያዚያ 1 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ መስከረም 30 ቀን 2017 ዓ.ም ሀገር አቀፍ የብክለት መግቻ ንቅናቄ መካሄዱ የሚታወስ ነው፡፡

የመሠረተ ልማት ግንባታዎችና የአካል ጉዳተኞች አካቶ ትግበራ

ዓለማየሁ ገዛው

ዜና ሐተታ

የአካል ጉዳተኞችና ዓይነስውራንን ቁጥር በተመለከተ በኢትዮጵያ የተሰራ የቅርብ ጥናት ባይኖርም፣ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ጥናቶች ከ20 ሚሊዮን በላይ አካል ጉዳተኞች በኢትዮጵያ እንደሚኖሩ ይጠቁማሉ። ይህ ቁጥር ከበርካታ ሀገራት አጠቃላይ የሕዝብ ቁጥር የበለጠ ነው። ይህም ሆኖ በኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ያላቸውን ቁጥር ያህል በበርካታ ጉዳዮች በቂ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል ማለት አይቻልም።

በሁሉም ዘርፍ አካታች ስራዎች በበቂ ሁኔታ እንዳልተሰሩ የአካል ጉዳተኛ ማህበራትና በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ የሚሰሩ የተለያዩ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች በብዙ አጋጣሚዎች ቅሬታ ያቀርባሉ። እነዚህን ቅሬታዎች ሙሉ በሙሉ የሚቀርፉ ባይሆኑም የአካል ጉዳተኞችን ጥያቄ ለመመለስ እንደሀገር የተሰሩና እየተሰሩ የሚገኙ ጥረቶችም ጥቂት አይደሉም።

አዲስ አበባን ጨምሮ በአብዛኞች የኢትዮጵያ ከተሞች በሚገነቡ ህንጻዎች፣ መንገዶች፣ አሳንሰሮች፣ ትራንስፖርትና ሆስፒታሎች ውስጥ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ መሰረተ ልማቶችን ከመስራት አኳያ ጥሩ ጅምሮች ቢኖሩም ብዙ ይቀራል። የአዲስ ህይወት ዓይነስውራን ማህበር ዋና ስራ አስኪያጅ አጸባዩሽ አበበ፣ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ አድርገው የሚሰሩት የመሰረተ ልማት ስራዎች በአንዳንድ አካባቢዎች ጥሩ ቢሆኑም በሁሉም ቦታ ወጥ እንዳልሆኑ፤ ለዚህም አብዛኞቹ መሰረተ ልማቶች በሚገነቡበት ወቅት በአሳንሰሮች፣ ሆስፒታሎችና መንገዶች ለአካል ጉዳተኞች ምቹና አስፈላጊው መስፈርት አለመሟላታቸውን እንደማሳያ ያነሳሉ ።

ችግሩን በምሳሌ ሲያብራሩም፣ በህንፃ መግቢያዎች፣ አሳንሰሮችና ሌሎች መወጣጫዎች ሁሉንም የአካል ጉዳት ያማከሉ ምልክቶች አለመኖራቸውን ይጠቁማሉ። በዚህም ምክንያት በቅርቡ ከሰባተኛ ወለል ላይ ወድቆ ህይወቱ ያለፈ ዓይነስውር መኖሩን ያስታውሳሉ።

በከተሞች አካባቢ በዋና መንገዶች ዙሪያ ጭምር ለተለያየ ግንባታና መሰረተ ልማት ስራዎች ተቆፍረው በአግባቡ ያልተደፈኑ በርካታ ጉድጓዶች መኖራቸውን የሚጠቁሙት ሥራ አስኪያጂ፣ ይህ ችግር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እየቀነሰ እንደሚገኝ፤ ችግሩ ግን አሁንም ለዓይነስውራን ፈተና እንደሆነ ይናገራሉ።

የሰርቫይቫልስ፣ ሪከቨሪና ሪሃብሊቴሽን ኦርጋናይዜሽን መስራችና ሥራ አስፈጻሚ አቶ በቀለ ጎንፋ በበኩላቸው፤ የአካል ጉዳተኞችን እንቅስቃሴዎች ምቹ ለማድረግ እንደሀገር አዋጆች መኖራቸውንና ኢትዮጵያም ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞችን ከንቨንሽኖችን መፈረሟን በማስታወስ፣ በሥራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች አማካኝነት አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ በየጊዜው

ደንቦችና መመሪያዎች እንደሚወጡ ያብራራሉ፡፡

እነዚህ ደንቦችና መመሪያዎች የሚገነቡ ህንጻዎች፣ መንገዶችና ድልድዮች አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ እንዲያደርጉ የሚያስገድዱ ናቸው። ይሁን እንጂ ተፈፃሚ እንዲሆኑ የሚደረገው ጥረት በቂ ነው የሚል እምነት የላቸውም። እንደ አቶ በቀለ ገለፃ፣ አሁን ላይ ከሚሰሩት መሰረተ ልማቶች ጋር ተያይዞ ከአካል ጉዳተኝነት አንፃር ብዙ ፈተናዎች አሉ። በከተሞች በሚካሄዱ በርካታ የህንጻ ግንባታ ስራዎች የአካል ጉዳተኞች መወጣጫዎች (ራምፖች) በአግባቡ እየተሰሩ አይደሉም። የሚሰሩትም ቢሆኑ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ወይም ለይስሙላ የሚሰሩ ናቸው።

መንግሥት በዚህ ረገድ ለህንጻዎች የአገልግሎት ፍቃድ በሚሰጥበት ወቅት እንዲህ አይነት ችግሮች ላይ ትኩረት በማድረግ የሚስተካከሉበት መንገድ መፍጠር አለበት። እነዚህን ችግሮች ለማቃለልም በቀጣይ አካል ጉዳተኞችን በተገቢውና ትክክለኛ መንገድ የሚያካትት ስራ ሊከናወን ይገባል ሲሉም ይናገራሉ።

አካል ጉዳተኞች ምቹ ባልሆኑ መሰረተ ልማቶች የሚደርስባቸውን ጉዳትና ጫና ለመቀነስ እንዲሁም ከተደራሽነት አኳያ ሆስፒታሎች፣ መንገዶች፣ ህንጻዎችና ትራንስፖርት ላይ ማህበራቸው ጥናቶች እንደሚሰራ ወይዘሮ አጸባዩሽ ይጠቁማሉ፡፡ በዚህም አካል ጉዳተኞችና ዓይነስውራን በሚሰሩባቸውና በሚንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች ከትራንስፖርት፣ ከመንገድ፣ ከሚሰሩበት ቦታ ጋር አመቺ አለመሆን ጋር ብዙ ፈተናዎችን እንደሚጋፈጡ ከጥናቶቹ ግኝቶች መገንዘብ እንደሚቻል ያመለክታሉ።

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ኅብረተሰቡ አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ የነበረው የተዛባ ግንዛቤ እየተቀየረ መምጣቱን ፣ በኢኮኖሚ ረገድ የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ግን አሁንም ብዙ ስራዎች እንደሚቀሩት ይናገራሉ፡፡ የአካል ጉዳተኞችን አካቶ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ሁሉም ማህበረሰብና መገናኛ ብዙኃን መስራት እንደሚጠበቅባቸው ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ በቀለ አስተያየት፣ በየትኛውም መንገድ አካል ጉዳተኞችን ያማከለ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር የወጡ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ኮንቬንሽኖችን ወደ ተግባር መቀየር ያስፈልጋል፡፡ በተለይም ከመሰረተ ልማት አኳያ ደረጃዎችና አሳንሰሮች ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ በሆነ መልኩ እንዲሰሩ ለመሐንዲሶችና ህንጻ ተቋራጮች ግንዛቤ ሊፈጠርላቸው ይገባል፡፡

የአዲስ አበባ ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የማህበራዊ ዘርፍ ኃላፊ ወይዘሮ ገነት ቅጣው፣ ቢሮው በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ በዳይሬክቶሬት ደረጃ ተሳታፊነትና አካታችነት ላይ እንደሚሰራ ይናገራሉ። በዚህም ሁሉንም የከተማ አስተዳደር ቢሮዎችን ከአካታችነት አንጻር ጠያቂ፣ ድጋፍ ሰጪና የተሰጣቸውን ኃላፊነት የማይፈጽሙትን ተጠያቂ የማድረግ ስራ እንደሚያከናውን ያብራራሉ። በተጨማሪም በከተማው የሚገነቡት መሰረተ ልማቶች አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረጉ እንዲሆኑ ከከተማው ፕላን እና ዲዛይን ቢሮ ጋር እየሰራ ድጋፍ፣ ክትትልና እርማት እንዲደረግ በጥናቶች ላይ ተመስርቶ ምክረ ሃሳብ ይሰጣል።

እንደ ኃላፊዋ ገለፃ፣ በአሁኑ ወቅት በከተማው በሚገነቡት ህንጻዎች ራምፖችና አሳንሰሮችን እንዲያካትቱ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡ ለአካል ጉዳተኞች የሚያስፈልጉትን መሰረታዊ ነገሮች የማያሟሉት ላይም በተቀመጠው የአሰራር ደንብና መመሪያ መሰረት ተጠያቂ ይደረጋሉ። አሁን በከተማዋ የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ቢሮዎች ለአካል ጉዳተኞች የተሻለ አካታችና ምቹ መሆናቸውን የሚናገሩት ወይዘሮ ገነት፣ ከዚህ በፊት የተገነቡት ህንጻዎች ጭምር ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የማድረግ ስራዎች እየተከናወነ ነው፡፡ አካል ጉዳተኞች በኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሙያና ስልጠና ማዕከላት ስልጠና ወስደው ወደ ስራ እንዲገቡም የሚያስችሉ ስራዎች አሉ።

ምሥራቅ አፍሪካን የማስተሳሰር ጉዞ

ምሕረት ሞገስ

ዜና ትንታኔ

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ለሚኖር ወዳጅነት እና የጋራ ተጠቃሚነት ከፍተኛ ትኩረት እየሰጠ ነው። ይህ ስትራቴጂካዊ የፖሊሲ አካሄድ የፖለቲካ ዲፕሎማሲ፣ የኢኮኖሚ ኢጋርነት፣ የጸጥታ ትብብር፣ የባህል ልውውጦች እና የአካባቢ ዘላቂ ግንኙነትን ጨምሮ የሁለትዮሽ እና ክልላዊ ትብብርን በተለያዩ መስኮች ማሳደግ ቅድሚያ የሚሰጥ ነው።

ኢትዮጵያ አካባቢያዊ ቀጣናዊ መረጋጋትን፣ የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረጉ የልማት ስራዎችን መስራት ፣ በተለይም ሰላምን በማስፈን ሀብቶችን ለጋራ ጥቅም ለመጠቀምና ለማልማት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላት በተደጋጋሚ አስታውቃለች። ለጉዳዩ ያላትን ቁርጠኝነትም በተጨባጭ አሳይታለች።

ለዚህም በማሳያነት የሚገለፀው የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን እያካሄደች ነው። በተለይም በኃይል አቅርቦት፣ በባቡር መስመር ግንባታ እና በንጹህ ውሃ አቅርቦት ዙሪያ ተጠቃሽ የሆኑ ሥራዎችን አከናውናለች፤ ለሱዳን፣ ለደቡብ ሱዳን፣ ለኬንያ እና ለጅቡቲ የኤሌክትሪክ ኃይል እያቀረበች ነው። ለጅቡቲ ንጹሕ የመጠጥ ውሃ እያቀረበች ትገኛለች።

ከሰላም አኳያም የሶማሌን ሰላም ለማረጋገጥ የከፈለችው መስዋእትነት እንዲሁም፤ ሱዳን እና ደቡብ ሱዳናውያን የውስጥ ችግራቸውን በሰላም እንዲፈቱ ሰፊ ጥረቶችን አድርጋለች፡፡ ሀገሪቱ የሰላም አስከባሪም አሰማርታለች።

በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የአውሮፓና የአሜሪካ ጉዳዮች ዳይሬክተር እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ ተንታኝ ዳርእስከዳር ታዬ(ዶ/ር) እንደሚናገሩት፤ ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገራት ማለትም ከምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት ጠንካራ ነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ አንደኛው ጎረቤት መሆናቸው በራሱ የግንኙነት አድማሱ በጣም ሰፊ እንዲሆን ያስገድዳል፡፡ እንደሩቅ ሀገሮች ለምሳሌ ኢትዮጵያ እና ኤሜሬት በጂኦግራፊ የተቀራረቡ አይደሉም፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ ከኤሜሬት ጋር ያላት ግንኙነት የተነጠለ ነው፡፡

የኢትዮጵያ እና የምሥራቅ አፍሪካ ግንኙነት ግን ከሩቅ ሀገሮች ከፍ ያለ ነው፡፡ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት፣ የማንነት ተመሳሳይነት ፣ ንግድ እና ድንበርን በጋራ ማስተዳደር አለ፡፡ የጋራ የድንበር ኮሚሽን አለ፡ ፡ ይህ በራሱ በግድም ሆነ በውድ የሚያስተሳስር ነው። ይህን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ኢትዮጵያ ደግሞ በልዩ ሁኔታ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ለጎረቤት ሀገራት ልዩ ትኩረት ሰጥታለች፡፡

በውጭ ጉዳይ ፖሊሲው በግልፅ እንደተቀመጠው ሁሉ፤ ኢትዮጵያ ምሥራቅ አፍሪካን በተለያየ መንገድ በማስተሳሰር በኩል ከፍተኛ ሚና እየተጫወተች ነው፡ ፡ ይህም ወደ ፊት ሀገሪቱን ስኬታማ እንደሚያደርጋት ይታመናል፡፡

በዋናነት እስከ አሁን በቀጣናው ሰላም ለማስፈን የከፈለችው ዋጋ ትልቅ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን በሀይል እና በመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታ ላይ እያደረገችው ያለው ተሳትፎ የሚበረታታ ነው። አሁን ላይም አካባቢውን በልማት እና በንግድ ለማስተሳሰር የጀመረችው ስራ ተስፋ ሰጪ እንደሆነም ጠቅመዋል።

ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይልን በስፋት ለማመንጨት መሥራት ከጀመረች አስር ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በእነዚህ ዓመታት ኤሌክትሪክ የማምረት አቅሟ በመጨመሩ ለኬንያ፣ ለሱዳን፣ ለጅቡቲ ማቅረብ ጀምራለች፡፡ ይህ ከፖለቲካ ነፃ በሆኑ በሰላም ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን፤ የልማት ሥራዎች የሚሠራበት ዕድል በኢትዮጵያ አማካኝነት እየሰፋ መምጣቱን የሚያመላክት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

የሀገሪቱ የኤሌክትሪክ ኃይል የማምረት አቅም እየጨመረ ሲሄድ ተቀራርቦ የመነጋገር አቅም እየጨመረ ይሄዳል፡፡ አሁን ላይ ከሱዳን ጋር ኢትዮጵያ ትልቅ ግብይት እያካሔደች ነው፡፡ ነዳጅን ጨምሮ ሽንኩርት ሳይቀር ከሱዳን ወደ ኢትዮጵያ እየገባ ነው፡፡ ከደቡብ ሱዳን ጋርም አሁን በመንገድ ለመተሳሰር ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ ይህም የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ያላቸውን ውስን ሀብት በጋራ የሚጠቀሙበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው ለማለት እንደሚያስደፍር አመልክተዋል፡፡

ለምሳሌ የኬንያ ኢንቨስትመንት ወደ ኢትዮጵያ እየመጣ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለዚህም ሳፋሪኮምን አንስተዋል፡፡ በቀጣይ በስፋት በባንክ እና በሌሎችም የንግድ ዘርፎች ኢትዮጵያ ውስጥ ለመሥራት ከፍተኛ ተነሳሽነት ማሳየታቸውንም ተናግረዋል፡፡

ዳርእስከዳር(ዶ/ር) እንዳብራሩት፤ ትስስር በሀገራቱ መካከል ከፍተኛ ግጭት እንዳይፈጠር ያስችላል፡፡ በምሳሌነትም ኢትዮጵያ እና ጅቡቲ ሁለቱም ተጠቃሚ በመሆናቸው እርስ በእርስ ጦርነት ውስጥ የመግባት ዕድላቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ እና ጅቡቲ ምንም ቢፈጠር ጦርነት ውስጥ ይገባሉ ብሎ ለመገመት አዳጋች ነው፡፡ ሁለቱም ጥቅማቸውን ላለማጣት ችግርን በውይይት ለመፍታት ጥረት ያደርጋሉ፡፡

ከኬንያ ጋርም በተመሳሳይ መልኩ ጦርነት የመፈጠር ዕድሉ ዝቅተኛ ነው፡፡ ባለፉት ጊዜያት ከሱዳን ጋር ብዙ ነገሮች ተፈጥረው ነበር፡፡ ነገር ግን ወደ ጦርነት አልተገባም፡፡ ምክንያቱም ሱዳን እና ኢትዮጵያ በብዙ መልኩ እርስ በእርስ ተሳስረዋል፡፡

በተጨማሪ የናይል ተፋሰስ ሀገራት ስምምነት ኮሚሽንን ለመመስረት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ሩዋንዳ ፣ ዑጋንዳ እና ደቡብ ሱዳን ተቀላቅለዋል። በቅርቡም ኮሚሽኑ ወደ ሥራ እንደሚገባ ይጠበቃል፡ ፡ይህ ቀጣናውን የማስተሳሰር የኢትዮጵያ ዕቅድ ቀስ በቀስ ፤ ሀገሪቱን እና ቀጣናውን ሊጠቅም በሚችል መልኩ እየሰፋ ይሄዳል፡፡ በቀጣናውም ለኢትዮጵያ ትልቁ ስኬት ይሆናል ብለዋል፡፡

ስራው ከተፅዕኖ እና ከጫና ነፃ እንዳልሆነ የሚናገሩት ዳርእስከዳር (ዶ/ር)፤ አሁን ላይ የተለያዩ አካላት በቀጣናው ፍላጎት እያሳዩ ነው፤ ትኩረትም እየሳበ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ሉብቻ መሥራት የሚቻልበት ሁኔታ እየተመናመነ መጥቷል። ይህም በሁሉም መስክ በጋራ መስራትን አስገዳጅ ያደርገዋል። ይህንን ታሳቢ ባደረገ መንገድም ሀገራችን እየተንቀሳቀሰች እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

አላስፈላጊ ጫናዎች ሲኖሩ ራሷን እያገለለችም ቢሆን፤ ሁኔታዎችን ተቋቁማ ሚናዋን ለመወጣት ጥረት በማድረግ ላይ ናት፡፡ ሶማሊያም ላይ የተከሰተው የዚህ እውነታ መገለጫ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባል አምባሳደር ዲና ሙፍቲ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ቀደም ሲልም ከምሥራቅ አፍሪካ ጀምሮ ነፃ ያልወጡ ሀገሮች ነፃ እንዲወጡ አፍሪካ ውስጥ ሰላም እንዲሠፍን መረጋጋት እንዲኖር ለምሳሌ በሶማሊያ እና በሱዳን ከፍተኛ ሚና ስትጫወት የቆየች ሀገር ናት፡፡

ቀድሞም ሆነ አሁን ኢትዮጵያ ምሥራቅ አፍሪካን በማስተሳሰር በኩል ያላት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይ የሕዝብ ለሕዝብ፣ የባህል እና የእምነት የመሳሰሉት ትስስር አላት፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ የወደፊት እጣ ፈንታ እና የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት እጣ ፈንታ በእጅጉ የተሳሰረ ነው፡፡

በተለይ አሁን በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ውስጥ ጎረቤት ሀገሮች ማለትም የአፍሪካ ቀንድ ወይም ከምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ጋር ያለን ግንኙነት በወታደራዊ፣ በማህበራዊ እና ፖለቲካዊ መስክ እጅግ በጣም መተሳሰር እንደሚያስፈልግ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ላይ ኢትዮጵያ በትጋት ሠርታለች፤ ወደ ፊትም ትሠራለች ብለዋል፡፡

ከምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ጋር የሁለትዮሽ ግንኙነቷን በማጠናከር እና በማስፋት የምሥራቅ አፍሪካ በይነ መንግሥታት ድርጅት (ኢጋድ) እንዲመሠረት እና እንዲጠናከር እንዲሁም ወደ ፊት በቀጣይነት ብዙ ሥራዎች እንዲሠሩ ኢትዮጵያ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገች ሀገር መሆኗን ጠቁመው፤ ወደፊትም በዚህ መልኩ ትቀጥላለች ብለዋል፡፡

እንደ ምሁራኑ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ከጎረቤቶቿ ጋር ተቀራርቦ ልማትን ለማከናወን እና ለምሥራቅ አፍሪካ ውህደት የበኩሏን አስተዋፅኦ ለማበርከት፣ አዎንታዊ የእድገት ውጤቶችን እና ዘላቂ ሰላም ለማምጣት እየሠራች ነው፡፡ በቀጣይም ትሠራለች።

በተለይ በቀጣይ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ሲጠናቀቅ ጎረቤት ሀገራት ከተጨማሪ የኃይል ሀብቶች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪ ከጎረቤቶቿ ጋር በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያላት ግንኙነት ሰፊና ጠንካራ እየሆነ ይቀጥላል፤ በቀጣናው ሀገራት መካከል መተባበር ፣ የጋራ ልማትን ማረጋገጥ እና ዘላቂ ሰላም መምጣቱ አዳጋች አይሆንም ብለዋል።

የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪው ፈተናዎች

ቤዛ እሸቱ

ዜና ትንታኔ

ሀገራት ወደ ውጭ የሚልኩት ምርትና ከውጭ የሚያስገቡት ምርት መመጣጠን እንደሚገባው የምጣኔ ሀብት ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ኢትዮጵያ የተኪ ምርት ስትራቴጂ ቀርፃ የሀገር ውስጥ ፍጆታን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት እየሰራች ትገኛለች። በስትራቴጂው ቅድሚያ የተሰጠው ደግሞ የአልባሳትና ጨርቃጨርቅ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በሀገር ውስጥ ምርት መሸፈን ነው፡፡ በዚህ ረገድ የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪው ተስፋ ሰጪ እምርታ ቢታይበትም ፈተናም ተጋርጦበታል።

በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማዕከል ተጠባባቂ ሥራ አስኪያጅ አቶ አላምረው አያልነህ፣ የጨርቃጨርቅና አልባሳት በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 30 በመቶ የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻ ወደ 60 በመቶ ለማድረስ እቅድ ተይዞ ያለፉትን አራት ዓመታት እየተሰራ እንደሚገኝ ይናገራሉ። በዚህም ጥረት ተስፋ ሰጪ እምርታዎች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አላምረው ገለጻ፤ ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ አራት የጨርቃጨርቅና አልባሳት ምርቶች ተለይተው ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ ለማምረት ጥረት እየተደረገ ነው። እነሱም የሀገር መከላከያና የሌሎች የጸጥታ አካላት አልባሳት፣ የተማሪ የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም)፣ የጅንስ ጨርቅና የጤና(ሜዲካል) ጋውን ናቸው፡፡

አሁን ላይ የሜዲካል ጋውን ፍላጎትን መቶ በመቶ በሀገር ውስጥ ምርት መሸፈን ተችሏል። 96 በመቶ የጸጥታ ኃይል አልባሳትንም በሀገር ውስጥ ማምረት ተችሏል። በእነዚህ አራት ምርቶች የተጀመረው ስትራቴጂክ ተኪ ምርት ባለፉት ሦስት ዓመታት ከ250 ሚሊዮን ዶላር በላይ ማዳን ተችሏል። በአራቱ ምርቶች



የተገኘውን ውጤት መነሻ በማድረግም አጠቃላይ የሀገሪቱ የተኪ ምርት ስትራቴጂ ተነድፏል ነው ያሉት፡፡

በስትራቴጂው 98 ያህል ምርቶች የተለዩ ሲሆን፤ በ2016 ዓ.ም 34 የጨርቃጨርቅ ምርቶች መመረት የሚችሉ መሆናቸውን በመለየት ወደ ተግባር ተገብቷል። ከዚህ ውስጥ በአጭር ጊዜ ሊተኩ የሚችሉ 15 የምርት አይነቶችን በመለየት የሦስት ዓመት የስትራቴጂው ማስፈጸሚያ መርሃግብር ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር መሸጋገሩን ተጠባባቂ ሥራ አስኪያጁ አብራርተዋል።

የጨርቃጨርቅና አልባሳትን ፍላጎት በሀገር ውስጥ የመተካት ጉዳይ ሲታሰብ አንዱ ፈተና በሸማቹ ዘንድ ያለው የተዛባ አስተሳሰብ ሲሆን፣ ሌላው በምርቶቹ ጥራት ላይ የሚነሳው ጥያቄ ነው። "በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ እኛም እንሸምት" በሚል መሪ ቃል ባለፉት ዓመታት እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ጨርቃጨርቅና አልባሳትን በሀገር ውስጥ በመተካት ረገድ ከፍተኛ ሚና ነበረው ይላሉ፡፡

እንቅስቃሴው ለሀገሩ ምርት የተሻለ እይታ ያለው ሸማች እንዲፈጠር እንዲሁም አምራቾች እንዲበረታቱ ማድረጉን ተጠባባቂ ሥራ አስኪያጁ ያስረዳሉ። እንዲሁም፣ የጨርቃጨርቅና አልባሳት ምርቶችን በሀገር ውስጥ ለመተካት ሲታሰብ ለገበያ የሚቀርቡት ምርቶች ጥራት ሊጠበቅ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አላምረው ማብራሪያ፤ ሳይንሱ በጥራት ማምረት ወጪ እንደሚቀንስ ያስቀምጣል። ይህም በተግባር የተረጋገጠ ነው። ይሁን እንጂ በአምራች ኢንዱስትሪዎች አካባቢ "የተሻለ ጥራት ያለው ምርት ቢመረት ብዙ ወጪ ስለማይወጣበትና ገበያው ይሄንን መሸከም አይችልም" በሚል በዝቅተኛ ጥራት አምርቶ ማቅረብ ይሻላል የሚል የተሳሳተ ግንዛቤና አመለካከት ይታያል፡፡ ይሄ ሊስተካከል የሚገባው መሰረታዊ ጉዳይ በመሆኑ በጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማዕከል ከሚከናወኑ ሥራዎች አንዱ ጥራትን ማምጣት የሚያስችሉ ሥልጠናዎች መኖራቸውን ይጠቁማሉ።

በየዓመቱ ከሁለት ሺ በላይ የኢንዱስትሪ ሠልጣኞችና ኢንዱስትሪውን የሚደግፉ አካላት በማእከሉ ሥልጠና እንደሚያገኙ የሚገልፁት አቶ አላምረው፤ ጥራት ያለው ጥሬ እቃ ከመምረጥ አንስቶ ጨርቃጨርቅና አልባሳት ተመርቶ ለተጠቃሚው እስከሚደርስ በምን መንገድ ጥራትን ማስጠበቅ እንደሚቻልና መሰል ሥልጠናዎች በማዕከሉ እንደሚሰጡ ተናግረዋል።

እንደ ተጠባባቂ ሥራ አስኪያጁ ገለጻ የኢንዱስትሪው ሌላ ፈተና ከንግድ ምልክትና ስያሜ(ብራንዲንግ) ጋር የተያያዘ ነው። ይህን ሲያብራሩም በብዙ ሀገራት አምራቾች ከጅምሩ የራሳቸውን ብራንድ ይዘው ወደ ገበያው እንደሚገቡ ያስረዳሉ። በዚህም የሀገር ውስጥ ድርሻቸውን አስፍተው በቀጣይ ታዋቂ ብራንድ ሆነው የሚወጡበትን የረዥም ጊዜ እቅድ በመንደፍ ይንቀሳቀሳሉ፡፡

"በሀገራችን ጨርቃጨርቅና አልባሳት አምራቾች ረገድ ያልተሰራበት አንዱ ይሄ የብራንዲንግ ጉዳይ ነው" የሚሉት አቶ አላምረው፤ በሌሎች ሀገራት የታወቀና ስሙን ያስተዋወቀን ብራንድ አስመስሎ በመስራት በአጭር ጊዜ ትርፍ ለማግኘት የማሰብ አዝማሚያ መኖሩን ይናገራሉ። በዚህም የራስን ስም ከመትከል ይልቅ የታወቁ ብራንዶችን አመሳስለው በመስራት ገበያ ላይ የሚታዩ አልባሳት መኖራቸውን በምሳሌነት ይጠቅሳሉ።

"ይሄ አካሄድ ኢንዱስትሪውን በዘላቂነት አያሻግርም" የሚሉት አቶ አላምረው፤ ከኢንዱስትሪ ፖሊሲውም ሆነ በተኪ ምርት ስትራቴጂ ከተያዘው የሀገር ውስጥ ምርትን የገበያ ድርሻ ማሳደግ ጋር አብሮ እንደማይሄድ ተናግረዋል።

ከዚህ አኳያ አምራቾች የራሳቸው የሆነ ብራንድ በመፍጠር ወደ ገበያው የሚገቡበትና የሚያሸንፉበትን ረዥም ራዕይ ኖሯቸው መስራት እንዳለባቸው ይመክራሉ። ለዚህ በራሳቸውም ብራንድ ምርታቸውን ለገበያ አቅርበው ውጤታማ የሆኑ የሀገር ውስጥ አምራቾችን እንዳሉ ማስተዋል ይገባል ባይ ናቸው።

በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ቴክኖሎጂ መምህር እያሱ ፈረደ እንደሚናገሩት፣ የሀገር ውስጥ አልባሳት የግብዓትና መሰል ችግሮች ጥራት ማጓደላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ሸማቾች ለሀገር

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

በክልሉ ከመኸር እርሻ ሦስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- በሲዳማ ክልል ከመኸር እርሻ ሦስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ መታቀዱን የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ገለጸ፡ ፡ በበጋ መስኖ ልማትም ከ11 ሚሊዮን በላይ ኩንታል የሆርቲካልቸር ምርት ለመሰብሰብ መታቀዱን ጠቁሟል፡፡

የሲዳማ ክልል የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ኃላፊ መምህሩ ሞኬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016/17 ዓ.ም የምርት ዘመን በዋና ዋና ሰብሎች ከለማው 106ሺህ ሄክታር በላይ መሬት ሶስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ ታቅዷል፡፡

የእርሻ ግብዓት አጠቃቀም፣የማሳ እንክብካቤ እና የሰብል ጥበቃ ስራዎች በከፍተኛ ጥንቃቄ መሰራታቸውን ተናግረው፤የመኸር ሰብል ብዙ ጊዜ ለተባይ እና ለበሽታ የተጋለጠ በመሆኑ ተጋላጭነት ለመቀነስ ከመጀመሪያው ጀምሮ በርካታ ሥራዎች መሰራታቸውን ገልጸዋል፡፡

በአሲዳማነት የተጋለጡ ቦታዎች 35 ሺህ ኩንታል ኖራ በመኸር እርሻ ጥቅም ላይ መዋሉን አውስተው፤ ከዚህ በፊት ጥቅም ላይ ከሚውለው 12ሺህ ኩንታል ጋር ሲነጻጸር ከእጥፍ በላይ ልዩነት እንዳለው አውስተዋል፡

ሥራዎች በከፍተኛ ጥንቃቄ የተሰሩ በመሆኑ እና ያጋጠሙ ችግሮችን መቆጣጠር በመቻሉ የታቀደውን ያህል ምርት ይሰበሰባል ተብሎ እንደሚጠበቅ የተናገሩት የቢሮ ኃላፊው፤ ከታህሳስ ወር መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ጥር ወር ድረስ ለሚዘልቀው የመኸር ምርት አሰባሰብ ዝግጅቶች መጠናቀቃቸውን ጠቁመዋል፡፡

በክልሉ ስነ ምህዳር አቀማመጥ ከፍ ያለ በመሆኑ ትልልቅ የምርት መሰብሰቢያ ማሽኖችን ማስገባት የማይመች በመሆኑ በእጅ የሚነተቱ አነስተኛ የሰብል መውቂያ ማሽኖች እንዲገቡ መደረጉን ያመላከቱት የቢሮ ኃላፊው፤ 30 የሰብል መውቂያ ማሽኖች በ15 ወረዳዎች የማሰራጨት ስራ መሰራቱን አመላክተዋል፡፡ 15 የወጣት ማህበራት ለስራው መዘጋጀታቸውንም አክለው ገልጸዋል፡፡

ጎን ለጎን በተጀመረው የበጋ መስኖ ሥራም በሆርቲ ካልቸር ምርቶች ላይ በትኩረት ለመስራት መታቀዱን ጠቁመው፤ በዓመቱ ከ72ሺ ሄክታር መሬት በላይ በመስኖ እንደሚለማ እና እስካሁን ከ22ሺ በላይ ሄክታር መሬት መልማቱን ጠቁመዋል፡፡

ለበጋ መስኖ ልማቱ አቅም ሊፈጥሩ የሚችሉ ከሁለት ሺህ 200 በላይ የውሃ ፓምፖች ከዚህ በፊት መሰራጨታቸውን የተናገሩት የቢሮ ኃላፊው፤ በዚህ ዓመት እጥረት ላለባቸው ወጣቶች እና ማህበራት 130 የውሃ ፓምፖች መሰራጨታቸውን አስረድተዋል፡፡

በበጋ መስኖ ልማት ከሚለማው 72ሺህ ሄክታር መሬት ከ11 ሚሊዮን በላይ ኩንታል የሆርቲካልቸር ምርቶች ለመሰብሰብ መታቀዱንም ገልጸዋል፡፡

በመስኖ በሚለማባቸው አካባቢዎች ብዙ ጊዜ በኩታ ገጠም እንደሚለማ ተናግረው፤ ከ80 በመቶ በላይ የመስኖ ገብ ማሳዎች በኩታ ገጠም እንደሚለሙ ተናግረዋል፡፡

ወቅቱ ምርት የሚሰበሰብበት በመሆኑ አርሶ አደሩ ምርት ሳይባክን የተለያዩ አካላትን በማስተባበር በጥንቃቄ እንዲሰበስብ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት...

ከ3ኛ ገጽ የዘረ

ውስጥ ምርት ዝቅተኛ ግምት መስጠታቸው በራሱ ችግር ነው፡፡

"ሸማቾች የሀገራቸው ምርት ጥራቱን ጠብቆ ሊሰራ ይችላል የሚል እሳቤ ሊኖራቸው ይገባልም" የሚሉት መምህሩ፤ በተመሳሳይ በአምራቾቹ ዘንድም የሀገር ውስጥ ሸማች ጥሩ ነገር ቢመረትም የመቀበል ሁኔታው ዝቅተኛ ነው የሚል ያልተገባ ፍረጃ መኖሩን ይጠቅሳሉ። በተጨማሪም አምራቾች አካባቢ ጥሩ ግብዓት ቢጠቀሙም ከስፌት ጀምሮ እያንዳንዱን ዝርዝር ነገሮች አስተካክሎ ከማዘጋጀት አንጻርና ልኬት በማመጣጠን ረገድ ክፍተት እንዳለ ነው የሚናገሩት።

ለዚህም በመስኩ ያሉት አብዛኞቹ ሰዎች በዘርፉ የሰለጠኑ አለመሆናቸው ምክንያት መሆኑን ያስቀምጣሉ፡፡ በአብዛኛው አልባሳትን ለማምረት ወደሥራ ዘርፉ የሚገቡት በጥቃቅንና አነስተኛ እንዲሁም በሌሎች የትምህርት መስኮች ተሰማርተው የነበሩ ሰዎች መሆናቸውንም በማሳያነት ይጠቅሳሉ። ይህም በዘርፉ ላይ ብዙ ጊዜ የሚሻገር ሥራ እንዳይሰሩና ወደሌላ የሥራ ዘርፍ ሲቀይሩ ማየት የተለመደ መሆን ተናግረዋል።

መምህር እያሱ ፈረደ ሲያብራሩ፣ በዘርፉ የተማረ የሰው ኃይል በሥራው ላይ ካለመሰማራቱ በተጨማሪ የቴክኖሎጂ፣ የግብአትና የገበያ እጥረት አለ ይላሉ። በተለይ ኢትዮጵያ ከአግዋ ከወጣች በኋላ የጥሩ ጥሬ እቃና የገበያ እጥረት መታየቱ የጥራት ችግር ፈጥሯል ባይ ናቸው፡፡

ሸማቾች ዘንድ የሚገዙትን አልባሳት ጥራት ከማየት ይልቅ ስም የማየት አዝማሚያ አለ የሚሉት መምህሩ፤ ይህም አምራቾች ተገቢ ባይሆንም የታወቁ ብራንዶችን አስመስለው ለመስራታቸው አንዱ ምክንያት መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡ ይህ በሀገራችን ሕግ ላያስጠይቅ ቢችል እንኳን ተገቢ አለመሆኑንና ባደጉት ሀገራት ከፍተኛ ቅጣት የሚያስከትል ወንጀል መሆኑን ጠቁመዋል።

ዓለም አቀፍ ስምምነቶችም አስመስሎ መሥራት ተጠያቂ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል። ተገቢ ባልሆነ አካሄድ የአንድ ጊዜ ትርፍ ከመፈለግ ይልቅ በራሳቸው ብራንድ ጥራት ያለው ምርት በማምረት በሂደት ማደግን ታሳቢ አድርገው መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ይመክራሉ፡፡

“በቀጣይ...

ከ1ኛ ገጽ የዘረ

ጎን ለጎን ጥቃት አድራሾችን መመዝገብ የሚያስችል ዲጂታል የመረጃ ሥርዓት ከድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመሆን እየጎለበተ ይገኛል፡፡ ጥቃት አድራሾች ጥቃቱን ሲፈጽሙ መረጃቸው ተመዝግቦ ከዲጂታል መታወቂያ ሥርዓቱ ጋር እንዲያያዝ እንደሚደረግም ጠቁመዋል፡፡

በቀጣይ በተደጋጋሚ ጥቃት የሚያደርስን ሰው መረጃው ለማህበረሰቡ በቅርበት እንዲደርሰው በማድረግ ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ከዛም ባለፈ አንዳንድ አገልግሎቶችን እንዳያገኝ የማድረግ ሥራዎች የሚሠሩበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ተናግረዋል፡፡

የሚለማው የዲጂታል ሥርዓት ጥቃት አድርሶ እንደተፈለገ መኖር እንደማይቻል እና ቀድሞ ማሰብ እንደሚገባ የሚያደርግ መተግበሪያ ነው። የማልማት ሥራውም ተጀምሯል፡፡ በዚህ ዓመት ይጠናቀቃል ብለዋል፡፡

የአቪዬሽን ዘርፉን...

ከ1ኛ ገጽ የዘረ

ባለሥልጣኑ ከ112 ሀገራት ጋር የሁለትዮሽ የአየር አገልግሎት ስምምነቶችን (BASA) ተፈራርሟል። እንዲሁም የኢትዮጵያን የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ የሚደግፍ ወሳኝ የቁጥጥር ማሕቀፍ አዘጋጅቷል ያሉት ዓለሙ (ዶ/ር)፤ ይህ ፖሊሲ ውጤታማ እንዲሆን ሁሉም የአፍሪካ ሀገራት ተባብረው እንዲሰሩ ጥሪ አቅርበዋል።

ይህም አፍሪካ ከዓለም አቀፉ የአቪዬሽን መረብ ጋር እንድትቀላቀል አስተዋፅኦ ያደርጋል። የአቪዬሽን ዘርፉንም በማሳደግ አዳዲስ እድሎችን መክፈት፣ ሥራ መፍጠር እና የአፍሪካን ኢኮኖሚ ማጠናከር እንደሚገባ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ቀልጣፋ የአየር ትራንስፖርትን ለማስተዋወቅ ከአጋር አካላት ጋር በቅርበት ለመሥራት ቁርጠኛ ነች ያሉት ሚኒስትሩ፤ የሚያጋጥሙትን ፈተናዎች ለማሸነፍ ዓለም አቀፍ ትብብር ቁልፍ ነው ብለን እናምናለን ነው ያሉት።

የኢትዮጵያ የሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ጌታቸው መንግስቴ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ሲቪል አቪዬሽን ኮሚሽን መስራች አባል መሆኗን ገልጸው፤ በአፍሪካና ከዚያም ባሻገር ትስስርን በማጎልበት በአቪዬሽን ዘርፍ አህጉራዊ ውህደትንና ትብብርን በመፍጠር ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውታለች ብለዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ እድገት የበኩሉን አስተዋፅኦ በማበርከት የአቪዬሽን ስነ-ምህዳር እድገትን በመደገፍ ቁልፍ ድጋፍ ማድረጉንም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የተመሰረተበትና የዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት ማቋቋሚያ ስምምነት የተፈረመበት 80ኛ ዓመት በዓል ከህዳር 30 እስከ ታህሳስ 3 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ በአዲስ አበባ ይካሄዳል፡፡ በበዓሉ አከባበርም የፓናል ውይይት፣ ዓለም አቀፍ የአቪዬሽን ቴክኖሎጂ አውደ ርዕይና ሌሎች ዝግጅቶች እንደሚከናወኑ ተጠቁሟል።

ለወሎ ተርሸሪ...

ከ1ኛ ገጽ የዘረ

ጽህፈት ቤቱ ዝግጁ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

የወሎ ዩኒቨርሲቲ በበኩሉ፤ የጽህፈት ቤቱ ሀብት በአግባቡ አዲት ተደርጎና አስፈላጊውን ሕግ ተከትሎ ከተከናወነ የሆስፒታሉን ግንባታ ተረክቦ ግንባታ ለማከናወን ዝግጁ መሆኑን አስታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሠረት ዳምጤ እንዳሉት፤ የሆስፒታሉን ግንባታ ሂደት የሚመራ የቦርድ አመራር ተሰይሟል፡፡ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤትም ተቋቁሟል፡፡ ከሕዝብ የተሰበሰበው ገንዘብ የታለመውን ፕሮጀክት ለመገንባት የሚያስችል እንዳልሆነ በመታመኑ ከ2010 ጀምሮ ለወሎ ሆስፒታል እንዲያስረክብ የቦርዱ የበላይ ጠባቂ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

ጽህፈት ቤቱ ለግንባታ የሚያስፈልገውን ገንዘብ በአይነት፣ በብር፣ በቶምቦላ ሎተሪና በሌሎችም መንገዶች ገቢ ለማሰባሰብ ጥረት አድርጓል፡፡ የሕዝብ ጥያቄ የተሰበሰበው ገንዘብ ምን ላይ ዋለ የሚል በመሆኑ ትኩረት ተደርጎ ኦዲት የተሠራው ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ መዋሉንና በአግባቡ ወደ ባንክ ገቢ መደረጉ ላይ ነው፤ ከኩፖን ቲኬት ሽያጭ የተገኘ 16 ሚሊዮን 43ሺህ 63 ብር እንዲሁም ከቶምቦላ ትኬት ሽያጭ የተገኘ 7 ነጥብ 7 ሚሊዮን ብር በድምሩ 23 ነጥብ 7 ሚሊዮን ብር ወደ ባንክ አልገባም ብለዋል፡፡

የሆስፒታሉ ግንባታ ቦርድ የመሠረዝ ስልጣን ሳይኖረው አንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን ትኬቶች የጠፉ በሚል ሰርዟል ብለዋል፡፡ በተለይ ባንክ ያልገባው ገንዘብ ለማን እንደተሰጠ ስለሚታወቅ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት አሰባስቦ ወደ ባንክ ማስገባት እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

ፕሮጀክት ጽህፈት ቤቱ ያለውን ሀብትና ንብረት ኦዲት አድርጎ ያስረከብ ሲባል እስከ 2010 በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባስልጣን ሕጋዊ እውቅና ነበረው፡፡ ከ2010 በኋላ አስረከቦ እንዲወጣ ስለተወሰነ ሕልውና ስለሌለው ምንም አይነት ወጪዎች መውጣት እንዳልነበረባቸው ጠቅሰው፤ ሆኖም ከ2010 እስከ 2016 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ድረስ 9 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ብር የሥራ ማስኬጃ ተብሎ ወጪ ሆኗል፡፡ አሁንም እየወጣ ሊሆን ስለሚችል መቆም እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

የሥራ አመራር ቦርዱ ጽህፈት ቤቱ ተዘግቶ ለወሎ ዩኒቨርሲቲ የማስረከቡ ሥራ እንዲከናወን መሥራት እንዳለበት አመላክተው፤ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣንም ያለውን ሀብት ኦዲት አድርጎ የሀብት ርክክብ ተደርጎ ጽህፈት ቤቱ እንዲዘጋ ማድረግ ይኖርበታል ብለዋል፡፡

የወሎ ዩኒቨርሲቲም የተሰጠው የሕዝብ አደራ ተቀብሎ የሆስፒታሉን ግንባታ አከናውኖ ለሕዝብ ጥቅም እንዲውል ማድረግ እንደሚገባው ጠቁመው፤ መንግሥትም ለግንባታው የሚውል የበጀት ድጋፍ ቢያደርግ የሚል አስተያየት አቅርበዋል፡፡

የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ወይዘሮ አራሬ ሞሲሳ በሰጡት የማጠቃለያ አስተያየት፤ ጉዳዩ የሕዝብ ጥያቄ በመሆኑ ተገቢ መልስ እንደሚያስፈልገው፤ በሂደቱ ለተፈጠሩ ክፍተቶች ተጠያቂ መሆን ያለባቸው አካላት ተጠያቂ መሆን እንደሚኖርባቸው አመልክተዋል፡፡

እስካሁን ባንክ ያልገቡ ብሮች በማን እጅ እንዳለና ለምን ባንክ ገቢ እንዳልተደረገ፣ ጽህፈት ቤቱ ሀብቱን አስረክቦ እንዲወጣ ከተወሰነ በኋላ እየወጣ ያለው ወጪ፣ ቦርዱም ባልተሰጠው ስልጣን ላይ ያደረገው የአዳ ስረዛ እና ሌሎችም የአሠርራር ጥሰቶች መታረም እና ተጠያቂ መሆን ያለበት አካል ተጠያቂ መደረግ እንደሚኖርበትም አሳስበዋል፡፡

በቀጣይነት ዋና ኦዲተር፣ የወሎ ዩኒቨርሲቲ፣ ቋሚ ኮሚቴው፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ የጽህፈት ቤቱ ኃላፊዎች እንዲሁም የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በተገኙበት ውይይት ተካሂዶ ውሳኔ ማግኘት እንዳለበት አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

ርዕሰ አንቀፅ

የሰላም አማራጭን መቀበል ለሕዝብ ፍላጎት መገዛት ነው!

በየትኛውም ሀገር እና ሕዝብ ታሪክ ውስጥ የተቃርኖ መንገዶችም ሆኑ ሀሳቦች የነበሩ፣ ያሉ እና የሚኖሩ ክስተቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ መነጋገርና መወያየት የችግሮቻቸው ሁሉ ቁልፍ ያደረጉ ሀገራትና ሕዝቦች የመኖራቸውን ያህል፤ በየምክንያቱ ጦር መማዘዝ የጀብደኝነትና የጉዳዮች ሁሉ መቋጫ አማራጭ አድርገው የሚከተሉ ቡድኖች በየሀገሩ ታይተዋል፤ እየታዩም ናቸው፡፡ ኢትዮጵያም እንዲሁ የእነዚህ ሁለት ተቃርኖ ሁነቶች መከሰቻም፤ መገለጫም ሆና ዘመናትን አሳልፋለች፡፡

በዚህ ረገድ በየዘመናቱ የሚነሱ የሕዝብ ጥያቄዎችን ማዕከል አድርገው የተከሰቱ የታሪክ ሁነቶችን መመልከት ይቻላል፡፡ በአንድ ወቅት የመደብ ጭቆናን፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትና የማንነት ጥያቄን፣ አለፍ ሲልም የፍትሃዊነት (በፖለቲካውም፣ በኢኮኖሚውም፣ በማኅበራዊ ጉዳዩም) አጀንዳን እንዲሁም የእውነተኛ ምላሽ ሰጪነት ነጥቦች የተነሱበት እና የተመለሱበትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

ምክንያቱም እነዚህ ክስተቶች የጨቋኝና ተጨቋኝ፣ የሰጪና ተቀባይ፣ የበዳይና ተበዳይ፣ የጠያቂና ተጠያቂ፣... እሳቤ የወለዳቸው፣ የእኛ እና የእነሱ ምልከታ የተጫናቸው፣ በጥቅሉ የባለቤትነት እና የእንግድነት መንፈስን የተላበሱ ስለነበሩ፤ አንዱ ባለ ጥያቄ ሆኖ ሌላው ጥያቄን መላሽ ተደርጎ የተሳለባቸው ነበሩ፡፡

ለዚህም ነው ጠያቂ ነኝ የሚለው አካል በየትኛውም የኃይል አማራጭ ጥያቄዬን አስመልሳለሁ ብሎ የሚነሳው፤ መላሽ የተባለውም ኃይል በጥያቄ ማስመለስ ሂደት የተሳተፉና ኃይልን አማራጭ ያደረጉ ቡድኖችን በኃይል ጨፍልቆ አደብ ለማስያዝ ሲተጋ የኖረው፡፡ በዚህ መልኩ የሚደረግ ጉዞ ደግሞ በአንድ ወቅት አንዱን አሸናፊ፣ በሌላኛው ወቅት ደግሞ ሌላኛውን የበላይ ሲያደርጉ ኖረዋል፡፡

ይሄን መሰሉ የኃይል ሚዛንን ማዕከል ያደረገ የጠያቂና ተጠያቂ፣ የመልስ ፈላጊና ምላሽ ሰጪ መንገዶች ታዲያ፤ ሕዝብን እንደ ሕዝብ፣ ሀገርንም እንደ ሀገር ዋጋ እያስከፈሉ በማያባራ ጠያቂነትና መልስ ፈላጊነት የታሪክ መንገድ ውስጥ አስገብተውን ዘልቀዋል፡፡ ዛሬም እንደ ሀገር እዚህም እዚያም የሚታዩ ግጭቶች፣ አለመረጋጋቶችና ጦርነቶች የዚሁ እሳቤ ቅጣያ ስለመሆናቸው እሙን ነው፡፡

ምክንያቱም የንጉሳውያኑን ሥርዓት ያስወገደው የሕዝብ ጥያቄን የማስመለስ አመጽና ግርግር ሥርዓቱን ቀይሮ አልተገታም፤ ይልቁንም ይዘቱን ለውጡ ንጉሳውያኑን የተካውን የደርግ ሥርዓትንም ሲፈትንና ሲሞግት ኖሯል፡፡ የደርግ ሥርዓትን የለወጠው ጥያቄም በዘመነ ኢህአዴግ በቃኝ አላለም፤ ይልቁንም በሕዝባዊ ማዕበል ፍትሃዊነትን ተነጥቄያለሁ ብሎ የ2010ሩን ሀገራዊ ለውጥ (ሪፎርም) ወለደ፡፡

ዛሬም ይሄ ጥያቄ አለኝ፣ መልስም እሻለሁ የሚለው ፍላጎትና እሳቤ ታዲያ እዚህም እዚያም በተለያዩ ቡድኖችና የግለሰብ ስብስቦች አዕምሮ ውስጥ መፈልፈሉ አልቀረም፡፡ ለዚህም ነው ከ2010ሩ ሀገራዊ ለውጥ ማግስትም ከጥቃቅን ረብሻዎች እስከ ሕልውና ጦርነት የደረሰ ቀውስ እንደ ሀገር የተከሰተው፡፡ አሁንም ድረስ በተወሰኑ ቡድኖችና አንጃዎች የሚመሩ አመጾች በአንዳንድ ክልሎች ቀጥለው የሚታዩት፡፡

እዚህ ጋ ሊታሰብና ልብ ሊባል የሚገባው ግን፣ እነዚህ አንጃዎች እዚህም እዚያም ግጭትና ጦርነትን የሚያውጁትና የሚመሩት እንዲመለስ የምንሻው የሕዝብ ጥያቄ አለን በሚል ምክንያት ነው፡፡ ነገር ግን ጥያቄዎቹ የሕዝብ ከሆኑ የሕዝብ ፍላጎት ጦርነት ወይስ ሰላም የሚለውን መገንዘብ እና ሕዝብ የሚፈልገውን መንገድ መከተል ይጠበቅባቸው ነበር፡፡

ከሰላም የሚያተርፈው ሕዝብ ነው፡፡ ከጦርነት የሚያተርፉት ደግሞ በጦርነት መንገድ ተጉዘው የሚነግዱ በሕዝብ ስም የግል ጥቅማቸውን ለማሳካት የሚታትሩ ቡድኖችና ግለሰቦች ናቸው፡፡ እናም ዛሬ ላይ ሀገርና ሕዝብ ስለ ሰላም ተደጋጋሚ ጥሪ እያደረጉ ባለበት ሁኔታ፤ መንግሥትም እንደ መንግሥት ችግሮችና ጥያቄዎች በሰላምና በውይይት ብቻ መፍትሄም ምላሽም እንዲያገኙ በጋራ ቁጭ ብለን እንወያይ እያለ ተደጋጋሚ ጥሪዎችን በሚያደርግበት ወቅት፤ ይሄንን ጥሪ ተቀብለውና የሰላምን ዋጋም ሆነ የሕዝብን ፍላጎት ተገንዝበው ለሰላም ጥሪው ምላሽ እየሰጡ ያሉ ቡድኖች በተበራከቱበት በዚህ ወቅት፤ ለሰላም መንገድ ጥሪው ጆሮ የሚነፍግ ኃይል ፍላጎቱ ሰላም፣ ዓላማውም የሕዝብ ጥያቄ ነው ለማለት አይቻልም፡፡

ጦርነትንና ኃይልን የችግሮች መፍቻ አድርጎ የወሰደ፤ በዚህም ነፍጥና ግርግርን እንደ አማራጭ ያደረገ ኃይል ሁሉ የሕዝብ ጥያቄ ምላሽ የሚያገኘው ከሰላምና ሰላም መንገድ ብቻ መሆኑን መገንዘብ ይኖርበታል፡፡ ወደዚህ መንገድ የገባው የሰላም መንገድ ተዘግቶብኝ ነው የሚል ምክንያት አለኝ ካለም፤ ዛሬ ላይ የሚደመጡ ዘርፈ ብዙ ድምጾች ይሄንን ምክንያት ቦታ የሚያሳጡ መሆናቸውንም በመረዳት፤ ለሰላም ቅድሚያ መስጠትና ያለ ቅድመ ሁኔታ ስለ ሰላም ለሚደመጡ ጽምጾች ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ መልኩ ለሰላም ምላሽ መስጠት ማለት ደግሞ የሕዝብን ፍላጎት መፈጸምና ለሕዝብ ፍላጎት መገዛት ስለሆነ፤ ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ዛሬም ለሰላም ጥሪዎች ጆሮም ጊዜም መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

ዋና አዘጋጅ
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ
ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ደህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

አሳሳቢው ቨርቹዋል ኦቲዝም

በቀምሳቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ከወደ ሀገረ አውስትራሊያ የተሰማው ሰሞነኛ ዜና በሀገሬም በሆነ ብዬ ተመኘሁ። አዎ አውስትራሊያ ከ16 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎች ማህበራዊ ሚዲያዎችን እንዳይጠቀሙ አግዳለች የሚለውን ብስራት ስሰማ በቨርቹዋል ኦቲዝም የምትሰቃየውን የእህቴን ልጅ አስታወሰኝ። እናቷም ሆነች አባቷ ገና ሁለት ዓመት ሳይሞላት ጀምሮ ከማጫወት ይልቅ የእጅ ስልካቸውን ሰጥተውና ቴሌቪዥን ከፍተው ስለሚተዋት ለዚህ ዘመን አመጣሽ የአእምሮ እክል ቨርቹዋል ኦቲዝም ዳርገዋታል። ያለ ጥፋቷ በወላጆቿ ስህተት ጤነኛ ሆና የተወለደች የምታሳሳ ህጻን ዛሬ በዚህ በሽታ የተነሳ ከእኩዮቿ የተለየች ህጻን ሆናለች።

ይቺ የእህቴ ልጅ ሶስት ዓመት ከመንፈቅ ቢሆናትም አፍ አልፈታችም። ከእኩዮቿና ከቤተሰብ ጋር ከመጫወት ይልቅ ስልክና ቴሌቪዥን ላይ ማፍጠጥን ትወዳለች። ስልክ ካልያዘች ወይም ቴሌቪዥን ካልተከፈተ ትቅበጠበጣለች። የምትይዘው የምትጨብጠው ይጠፋታል። ስልክ ስትቀማ ደግሞ ምርር ብላ ስለምታለቅስ እና በሌላ ነገር ልትደለል ስለማትችል ስልክ ተመልሶ ይሰጣታል። ስልክ ከያዘች ቴሌቪዥን ከተከፈተላት ስለአባት ስለ እናቷ ግድ የላትም። ምግብ እንኳ በቅጡ አትበላም። እያደር እየዋል ባህሪዋ ወጣ እያለና እንግዳ እየሆነ መጣ።

አፍ ባለመፍታቷና ባህሪዋ እንደ እኩዮቿ ባለመሆኗ ወላጆቿ ለሥነ ልቦና ጫና ተዳርገዋል። አዎ እንደ ሌሎች እኩዮቿ በኮልታፋ አንደበቷ አታወራቸውም። አባቢ እማሚ ብላ አትጠራቸውም። ሥራ ውሎ የሚገባ አባቷን በናፍቆት አትቀበለውም። ከእሱ ይልቅ ስልኩን ለመቀበል ትጓጓለች። ጎረቤትም ቤተ ዘመድም ምነው እስካሁን አፍ ሳትፈታ ብሎ በጠየቀ ቁጥር እናትም አባትም መሸማቀቃቸው አልቀረም። አፍ አውጥተው ባይናገሩም በጥፋተኝነት ስሜትና በጸጸት እየተሰቃዩ መሆኑን ለመገንዘብ ሞራ ገላጭ መሆን አያስፈልገም። ሁለተኛዋ ልጅ ስትወለድ ተመሳሳይ ችግር እንዳይከሰት ወትውቼ ወትውቼ ስልክና ቴሌቪዥን በአጠገቧ እንዳይደርስ በመደረጉ ከፈጣሪ ጋር የታላቅ እህቷ እጣ ፈንታ እንዳይገጥማት እየተደረገ ነው። ወደ ነገረ አውስትራሊያ ስመለስ፤

አውስትራሊያ ከ16 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎች ማህበራዊ ሚዲያዎችን እንዳይጠቀሙ የሚያግደውን ሕግ በፓርላማ አፅድቃለች፡፡ በውሳኔው መሠረትም በሀገሪቱ እድሜያቸው ከ16 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎች የቲክቶክ፣ ስናፕ ቻት፣ ፌስቡክ፣ ሬዲት፣ ትዊተር (ኤክስ) እና ኢንስታግራም አካውንት መክፈት አይችሉም፡፡ ከላይ የተጠቀሱት የማህበራዊ ትስስር ገፆች ታዳጊዎች አካውንት እንዲከፍቱ የሚፈቅዱ ከሆኑ 50 ሚሊዮን የአውስትራሊያ ዶላር ቅጣት እንደሚጠብቃቸው መንግሥት አስጠንቅቋል።

የአውስትራሊያ መንግሥት ኮሙኒኬሽን ሚኒስትር ሚሸል ሮውላንድ በሀገሪቱ ሰፊ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ድጋፍ ያገኘው ይህ ውሳኔ የታዳጊዎችን ደህንነት ለመጠበቅ ያለመ መሆኑን፤ በአውስትራሊያ እድሜያቸው ከ14 እስከ 17 ዓመት የሆኑ ታዳጊዎች ጎጂ ይዘት ያላቸውን ጉዳዮች በማህበራዊ ትስስር ገፆች ሲመለከቱ እንደነበር አስታውሰው፤ ከልከላው ታዳጊዎች በማህበራዊ ሚዲያዎች የሚደርስባቸውን ጫና ይቀንሳል ብለዋል፡፡

ከአውስትራሊያ አስቀድማ ስፔን ባለፈው ሰኔ ወር ከ14 እስከ 16 ዓመት ያሉ ታዳጊዎች ማህበራዊ ሚዲያዎችን እንዳይጠቀሙ መከልከሏ ይታወቃል። በአሜሪካም በተወሰኑ ግዛቶች ላይ ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል መባሉን አልጀዚራ ዘግቧል፡፡ ለመሆኑ ኦቲዝም ምንድነው? ቨርቹዋል ኦቲዝምስ ? ቆየት ካለ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ያገኘሁትን ብያኔ ላጋራችሁና ልመለስ።

ኦቲዝም የሚለው ቃል የግሪክ ሲሆን ፍቺውም "ብቸኛ" የሚል ነው። ምክንያቱ ደግሞ ኦቲዝም (በሙሉ ስሙ ኦቲዝም ስፔክትረም ዲስኦርደር) ያለባቸው ልጆች ከሌሎች ልጆች ጋር የማይቀላቀሉ፣ የሚረዳቸው ሰው ካላገኙ በቀር ማንም ሊረዳቸው ስለማይችል ብቸኛ ይሆናሉ። ኦቲዝም ያለባቸው ልጆች ኦቲስቲክ ይባላሉ። እነዚህ ልጆች የራሳቸው ዓለም ያላቸው ስለሆኑ የሚረዳቸው ሰው ይፈልጋሉ። የማያቋርጥ ክትትል ይጠይቃሉ።

በሀገራችን አብዛኛው ሕዝብ ስለ ኦቲዝም ብዙም ዕውቀት ስለሌለው ብዙዎቹ የዚህ በሽታ ተጠቂዎች ከማኅበረሰቡ ይገለላሉ። አንዳንድ ወላጆች ስለሚያፍሩባቸው ከቤት ስለማያስወጧቸው፣ አንዳንዶቹ ባለመረዳት መንፈስ ወይም አጋንንት አለባቸው በሚል የተሳሳተ ምልከታ ምክንያት በማሰር ያሰቃዩአቸዋል። ኦቲዝም ልክ እንደ ጨጓራ ቁስለት ወይም ኩላሊት ህመም እንጂ ሌላ አይደለም። የአዕምሮ መዛባት ችግር (disorder) ነው

በሀገራችን አብዛኛው ሕዝብ ስለ ኦቲዝም ብዙም ዕውቀት ስለሌለው ብዙዎቹ የዚህ በሽታ ተጠቂዎች ከማኅበረሰቡ ይገለላሉ። አንዳንድ ወላጆች ስለሚያፍሩባቸው ከቤት ስለማያስወጧቸው፣ አንዳንዶቹ ባለመረዳት መንፈስ ወይም አጋንንት አለባቸው በሚል የተሳሳተ ምልከታ ምክንያት በማሰር ያሰቃዩአቸዋል። ኦቲዝም ልክ እንደ ጨጓራ ቁስለት ወይም ኩላሊት ህመም እንጂ ሌላ አይደለም። የአዕምሮ መዛባት ችግር (disorder) ነው። ማወቅ ያለብን ነገር ኦቲስቲክ የሆነ ልጅ ማንም ሰው አጭር ወይም ጠይም ሆኖ እንደተፈጠረው ተፈጥሯዊ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ማኅበረሰብ ያንን መረዳት አለበት።

ኦቲዝም በሽታ ቢሆንም ኦቲስቲክ ያለባቸውን ልጆች ፍቅር፣ ትዕግስትና ጊዜ ከሰጠናቸው ከሰው ጋር ወደ መግባባት ወደ መሻሻል ይመጣሉ። ማኅበረሰቡ ያንን አውቆ ከታገሰ በየቤታችን፣ በየሰፈራችን በዚህ በሽታ የተያዙ ልጆችን ልንረዳቸውና ልናሽላቸው እንችላለን። ፍቅር፣ ትዕግስትና ጊዜ ግን ይፈልጋሉ።

ሰዎች መረዳት ያለባቸው ነገር ኦቲዝም ክትትል

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

ነፃ ሃሳብ

ደህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ሳይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኃን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

አሳሳቢው ቨርቹዋል...

ከገጽ 5 የዞረ

ካገኘ መሻሻልን የሚያመጣ ሲሆን ዳውን ሲንድሮም ግን ከዘረመል መዛባት /genetic disorder/ (ወይም ደግሞ የክሮሞዞም ከተለመደው ውጪ መሆን /chromosome abo=normality/) ምክንያት የአዕምሮ እድገት ውስንነት ነው። የሚወለዱ ልጆች ለዳውን ሲንድሮም የመጋለጣቸው ዕድል ከእናቶች ዕድሜ ጋር ተያያዥነት አለው። በአሃዝ ለማስቀመጥ ያህል፥ ዕድሜዋ 25 ዓመት የሆነች እናት ልጇ ለዳውን ሲንድሮም የመጋለጥ ዕድሉ ከ1,250 አንድ ብቻ ሲሆን፥ ዕድሜዋ 40 ዓመት የሆናት እናት ግን ልጇ ለዳውን ሲንድሮም የመጋለጥ ዕድሉ ከ100 አንድ አካባቢ ነው (ምንጭ)።

የእንግሊዝና የጣሊያን ተመራማሪዎች በጋራ ባደረጉት ጥናት እንደገለጹት አስቀድሞ የኦቲዝም ተጠቂዎችን ለመለየት የሚያስችል የደምና የሽንት ምርመራ በሕፃናት ላይ በማድረግ ለኦቲዝም ሕክምና መስጠት የሚቻልበት ደረጃ ላይ እየደረሱ መሆኑን በቅርብ ጊዜ ተዘግቦ ነበር (ምንጭ)። ሕፃናት የኦቲዝም ተጠቂ መሆናቸውን ለማወቅ በደም ውስጥ የሚገኝ የፕሮቲን መጠንን በመለካት ማወቅ እንደሚቻልም ጥናቶች ያረጋግጣሉ። የኦቲዝም ተጠቂ የሆኑትንና ያልሆኑትን ሕፃናት በማነጻጸር በተደረገው የሽንትና የደም ናሙና ምርመራ በኦቲዝም የተጠቁት ሕፃናት ከፍ ያለ የፕሮቲን ጉዳት እንደታየባቸውና በኦቲዝም ያልተጠቁት ደግሞ የተሻለ የፕሮቲን ስብጥር በደማቸው መገኘቱን ገልጸዋል። ሕፃናት በደማቸው አነስተኛ የፕሮቲን ስብጥር በሚኖርበት ጊዜ ለኦቲዝም የመጋለጥ ዕድላቸውን እንዲሰፋ ያደርገዋል።

ኦቲዝም ከፍተኛ የሆነ የአዕምሮ ዕድገት ውስንነትን በማምጣት በሰው ሥነ ባህርይ ላይ ጉዳት በማድረስ በማኅበራዊ ሕይወት ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል። ከዓመታት በፊት በአምስት ሀገራት የተደረገ ትልቅ ጥናት እንደሚያመለክተው 80 በመቶ ለኦቲዝም የተጋለጡ ሕፃናት በዘር የተላለፈባቸው እንደሆኑ ያመላክታል። ሌላ የብዙ ጥናቶች ውሁድ ጥናት (meta-analysis) እንደሚያሳየው ደግሞ በዘር በመተላለፍ ለኦቲዝም የመጋለጥ ዕድል ከ60 እስከ 91 በመቶ ሲሆን፥ በሥነ ሕይወት እና አካባቢ ምክንያት (environmental factors) ለኦቲዝም የመጋለጥ ዕድልም አሌ የማይባል እንደሆነ ያስረዳል።

ኦቲዝም ትልቅ የጤና ጉዳይ ነው፤ ከቀላል ምልክት እስከ ጥልቅ እና በጣም ከባድ የሆነ የጤና እክል ነው። በሽታው በአእምሮ ዘገምተኛ ሕፃናት እና በደንብ ባደጉ የአካዳሚክ ክህሎት ባላቸው ሰዎች ላይ እንደሚገኝ ኦቲዝምን የሚከታተሉ የሕክምና ባለሙያዎች ይናገራሉ። የመጀመሪያዎቹ የኦቲዝም ምልክቶች በጣም ቀደም ብለው ይታያሉ፤ ብዙውን ጊዜ ከአስራ ሁለት ወራት በላይ በሆኑ ሕፃናት ላይ ይታያሉ፤ እንዲሁም ከሶስት ዓመት በፊት በግልጽ ይታያሉ።

በልጅ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ምልክቶች ብዙውን ጊዜ በወላጆች ይስተዋላሉ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ቀድሞውኑ በጨቅላነታቸው ሕፃኑ በጣም ጨዋ፣ የሚያያቸው ሰዎች ላይ የማያተኩር፣ እና ሲያነሱት ጠንካራ ነው። በተጨማሪም ሕፃኑ በአንድ ነገር ላይ ለሰዓታት ያተኩራል፤ ለምሳሌ አይጮኽም ወይም ንግግር አያዳብርም። በተጨማሪም የልጁ እድገት መጀመሪያ ላይ መደበኛ እና ያልተለመዱ ባህሪያት በድንገት ሊከሰቱ ይችላሉ።

ኦቲዝም በማኅበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ ሁከት ይፈጥራል። የኦቲዝም ልጆች ብዙውን ጊዜ አይታዩም፣ ለምሳሌ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር የዓይን ለዓይን ግንኙነት (eye contact) አይፈጥሩም፤ አሊያም ቢፈጠሩም በጣም ለአጭር ጊዜ ነው። ኦቲስቲክ ልጅ እንደ ታመመ ብቻውን ጊዜ ማሳለፍ ይመርጣል። አንዳንድ ጊዜ አይታየኝም እና አይሰማኝም የሚል ስሜት ይሰማቸዋል።

ወደ ቨርቹዋል ኦቲዝም ስንመጣ ከሁለት ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት በብዛት ስክሪን እንደ ቴሌቪዥን፣ ስልክ ፣ ታብሌት የመሳሰሉትን በብዛት በመጠቀም የሚፈጥረ የአእምሮ ችግር ነው። ወጣ ያሉ ባህሪዎችን፤ የመግባባት ውስንነቶችን፤ እረፍት የለሽ መሆን ፤ትኩረት ማድረግ አለመቻል፤ ጨዋታዎች ላይ ፍላጎት መቀነስ፤ ማህበራዊ መስተጋብር ወይም ተግባቦት አለመኖር፤ ተለዋዋጭ ስሜት፤ የመረዳት እክል፤ አፍ የመፍታት ወይም የንግግር እና ቋንቋ መዘግየት፤ የተገደበ የዓይን ግንኙነት፤ ወዘተረፈ ከቨርቹዋል ኦቲዝም ምልክቶች ጥቂቶች ናቸው። የሚያሳዝነው እነዚህ ሁሉ ባህሪዎች በእህቴ ልጅ ላይ ይታያሉ።

የቪርቹዋል ኦቲዝም ህመምን በባህርይ እና የስፒች ቴራፒ፤ ልጆች ስክሪን ላይ የሚያጠፉትን ጊዜ በማቆም፤ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን በመጨመር፤ ፊት ለፊት የሚናገሩበትን መንገድ በመፍጠርና በማስተዋወቅ፣ ወዘተረፈ ማስተካከል ይቻላል። ከዚህ ጎን ለጎን ህጻናትንና ታዳጊዎችን ከማህበራዊ ሚዲያ የሚጠብቅ ሕግ ሊወጣ ይገባል። ይሄን ለማለት መግፍኤ የሆኑኝን ነጥቦች መለስ ብዬ ላነሳሳ።

አሁን አሁን ልጆች ከእኩዮቻቸው ጋር ጭቃ አቡክቶ ቦርቆ ከመጫወት ይልቅ ቴሌቪዥንና እጅ ስልክ ላይ መጣድን ይመርጣሉ። ቀደም ባለ አንድ መጣጥፌ ለመግለጽ እንደሞከርሁት፤ እኔ በምኖርበት የጋራ መኖሪያ ቤት ቅዳሜና እሁድ ሆነ በአዘቦት ከትምህርት ቤት ሲመለሱ በእረፍታቸው ውጭ ወጥተው ሲጫወቱ አላይም ። ድንገት መብራት ሲጠፋ ግን ቴሌቪዥን ስለሚቋረጥ ፣ ብሮድ ባንዱም ስለማይሠራ ከየቤታቸው መውጣትና ሰፈሩን መቀወጥ ይጀምራሉ ። በዚህ መሃል መብራት ከመጣ ሰፈሩን በጩኸትና በፉጨት ያደበላልቁና ወደየቤታቸው ይመለሱና ሰፈሩ መልሶ ጭር ይላል ። ሩጦና ዘሎ ያላደገ ህጻን አካላዊም አእምሯዊ ብቃቱ ላይ የሚያመጣውን ተጽዕኖ ለአፍታ አስቡት ።

የእጅ ስልክ ምርኮኛ እየሆኑ ነው ። ዘመድ ቤት ሲመጣም ሆነ እናንተ ዘመድ ጥያቄ ስትሔዱ ሁለት ዓመት ያልሞላቸው ህጻናት ሳይቀሩ ጠጋ ብለው የእጅ ስልክን ተቀብለው ከአንድ አንድ ጌም ፍለጋ ነው የሚገቡት። ሶስት ዓመት ያለፋት የእህቴ ልጅ ቤት ስትመጣ ስልኬን ለመቀበል ነው የምትሽቀዳደመው። መጣጥፎችን በእጅ ስልኬ ስለምጽፍና ብዙ ዶክመንት ስለሚይዝ ታጠፋብኛለች ብዬ ስለምፈራ ስለማልሰጣት ሁል ጊዜ በመጣች ቁጥር ጸብ ነው። ስታለቅስ ሌላ ስልክ ሰጥተው ያባብሏታል።

ልጅ ሲያለቅስ በከረሜላ በቼኮላት ሳይሆን የሚደለለው በስልክ ሆኗል ። ይህ የስልክ ፍቅር አብሮ ያድግና ከፍ ሲሉ ስልክ ካልተገዛልን ከወላጅ ጋር ጸብ ነው ። መቼም ወላጅ የሚኖረው ለልጆቹ ነውና እነሱን ለማስደሰት ቢያጣም ተበድሮና ተለቅቶ ገዝቶ መስጠቱ አይቀርም ። ስልኩን ገዝቶ ይስጥ እንጂ አጠቃቀሙ ላይ ቁጥጥር ስለማያደርግ ልጆቹ በጌምና እንደ ቲክቶክ ባሉ የማህበራዊ ሚዲያ ሱስ ይጠመዳሉ ። ለከፉ ሌሎች አደጋዎችም ሊጋለጡ ይችላሉ ። ሱሱ ያድግና ለተለያዩ የአእምሮ ሕመሞች ይዳርጋቸዋል ።

ለጭንቀት ፣ ለድብርት ፣ ራስን ለመጥላትና ራስን ለማጥፋት ይጋለጣሉ። ዛሬ ልጅን አሳድጎ ለወግ ለማዕረግ ማብቃት ፈታኝ እየሆነ ነው። ልጆቻችን ከእጃችን እያመለጡን ነው ። ከእድሜያቸው ቀድመው ለተለያዩ እኩይ ተግባራት እየተጋለጡ ነው። ችግሩ ዓለምአቀፋዊ ነው። መጠኑ ይለያይ እንጂ ምዕራባውያን በዚህ

ልጅ ሲያለቅስ በከረሜላ በቼኮላት ሳይሆን የሚደለለው በስልክ ሆኗል። ይህ የስልክ ፍቅር አብሮ ያድግና ከፍ ሲሉ ስልክ ካልተገዛልን ከወላጅ ጋር ጸብ ነው ። መቼም ወላጅ የሚኖረው ለልጆቹ ነውና እነሱን ለማስደሰት ቢያጣም ተበድሮና ተለቅቶ ገዝቶ መስጠቱ አይቀርም

እየተፈተኑ ነው ። ቢቸግራቸው ማህበራዊ ሚዲያዎች የእድሜ ገደብና የይዘት ክልከላ እንዲያደርጉ ግፊት ቢያደርጉም የተጠበቀውን ያህል ውጤታማ ስላልሆነ ከእነ አካቴው ይታገዱ እስከማለት ደርሰዋል። ይሄን ውትወታ ታዋቂ ሰዎች ሳይቀሩ እየተቀላቀሉት ይገኛል።

ፋሪድ ዘካሪያ በዋሽንግተን ፖስት መጣጥፉ፤ “የሁለት ሴት ልጆች አባት ስለሆንሁ ግማሹ ልቤ ቲክቶክ ቢታገድ ይለኛል ። በሚያስፈራ ሁኔታ ሱስ አስያዥ ስለሆነ። በአሜሪካ 150 ሚሊዮን ሰዎች የቲክቶክ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ ፤ ከሶስቱ ተጠቃሚዎች ሁለቱ ነፍስ ያላወቁ ብላቴናዎች ወይም ልጆች ናቸው።

ልጆች ለቲክቶክ ሱስና ለአእምሮ በሽታዎች ማለትም ለጭንቀት ፣ ለድባቴ ፣ ራስን ለማጥፋት ለሚገፋፋ ስሜት እየተዳረጉ ነው። አሜሪካውያንን ጨምሮ በመላው ዓለም የሚገኙ የሥነ አእምሮ ሊቃውንትና ፖለቲከኞች ከቲክቶክ ጋር በተያያዘም ሆነ ስለተቀረው ማህበራዊ ሚዲያ ልጓም ለቆ ቼ ፈረሴ ይቁም ። ሳይቃጠል በቅጠልን እየለፈፉ ነው ። እኔም ሀገራችን ህጻናትንና ታዳጊዎችን ማህበራዊ ሚዲያ እንዳይጠቀሙ የሚከለክል ወይም የሚገድብ ሕግ እንድታወጣ እጠይቃለሁ።

በተለይ ልጆችን ለሱስና ለአዕምሮ ሕመም እየዳረገ ስላለው የማኅበራዊ ሚዲያና አንድምታው ላንሳ። በአሜሪካው ነጩ ቤተ መንግሥት የሕዝብ ጤና ተጠሪው ወይም ሰርጀን ጄነራል ዶ/ር ቪቬክ ሙርዚ የልጆችንና የወጣቶችን የማኅበራዊ ሚዲያ ሱስ የወቅቱ የሕዝብ የጤና ቀውስ ይሉታል ።ዶ/ር ቪቬክ በአደባባይ ወጥተው፤ “እንደ ኢንስታግራምና ቲክቶክ ባሉ ማኅበራዊ ሚዲያዎች የተነሳ የልጆቻችን የአዕምሮ ጤና ጉዳይ በብርቱ ያሳስበኛል።” ሲሉ ለመንግሥታቸውም ሆነ ለአሜሪካውያን የማንቂያ ደወሉን አሰምተዋል።

ፋሪድ ዘካሪያ በ”ዋሽንግተን ፖስት”ጋዜጣ ፣ “Why banning TikTok won’t do any good” ወይም “ቲክቶክን ማገድ ለምን ፋይዳ ቢስ ይሆናል” በሚል ርዕስ ባስነበበን የግል አስተያየቱ፤ ስለ ቲክቶክ ባሰብሁ ቁጥር ይበልጥ ያስፈራኛል የሚለው ፋሪድ ዘካሪያ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለተከታታይ ሁለት እሁዶች በዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣም ሆነ በCNN/GPS ጽፎ አያውቅም። ባልተለመደና ተከታዮቹን ባስገረመ ሁኔታ ስለ ቲክቶክ ግን ጻፈ።

ይህ የቻይናው መተግበሪያ አሜሪካንን እንዴት እንዳሳሰባትና እረፍት እንደነሳት ጥሩ ማሳያ ነው። ፋሪድ፣ ባለፈው ሳምንት የቲክቶክን መታገድ ተቃውሜ ሞግቼ ነበር ይለንና። ከተለያዩ ሰዎች ጋር ባደረግሁት ውይይት የተገነዘብሁት ነገር ቢኖር፤ የአሜሪካውያን ዋና ስጋት ቲክቶክ የቻይናዊ ንብረት መሆኑ ሳይሆን ከየትኛውም ማኅበራዊ ሚዲያ በላይ አደገኛ ሱስ አስያዥ መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ ሁላችንን እያሳሰበን ያለ ጉዳይ ስለሆነ ሳንዘገይ አንድ ነገር ማድረግ አለብን።

አሜሪካውያን በ2022 ዓ.ም ከሁሉም የማኅበራዊ ሚዲያ መተግበሪያዎች በአንደኛ ደረጃነት ቲክቶክን አውርደዋል። ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑ የአሜሪካ ብላቴናዎች ወይም ታዳጊ ልጆች ቲክቶክን ይጠቀማሉ። ከስድስቱ አንዱ ደግሞ በቲክቶክ ሱስ ተለክፈዋል። በሀገራችንም በጥናት ባይረጋገጥም ህጻናትንና ታዳጊዎችን ሱሰኛ እያደረገ መሆኑ የአደባባይ ሀቅ ከሆነ ሰነበተ። አበው እመው ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ የሀገራችን ህጻናትም ከዚህ ዘመን አመጣሽ ወረርሽኝ መጠበቅ ስላለባቸው በጥናት ላይ የተመሠረተ የማህበራዊ ሚዲያ ገደብና ክልከላ ሊደረግ ይገባል።

ሻሎም ! አሜን ።

ኢኮኖሚ

ሳይንስና ቴክኖሎጂ

በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ሦስት ብስክሌቶች የሠራው የፈጠራ ባለሙያ

ወርቅነሽ ደምሰው

የአርሶ አደር ልጅ ነው፤ ወላጆቹ የሚተዳደሩበትን የግብርና ሥራ እየሠራ አድጓል። ወላጆቹ የእነርሱን ፈለግ እንዲከተል ቢገፋፉትም የሕይወት ጥሪው ግን ሌላ ነበር፤ አብዛኛውን ጊዜውን በቴክኒክ ሥራዎች ላይ በመሳተፍ የልጅነት ጊዜውን አሳልፏል።

ተሰጥኦውን ልብ ብለው ያስተዋሉና የተረዱ አንዳንድ የአካባቢው ሰዎች ወላጆቹን መክረው ወደ ትምህርት ቤት እንዲገባ አደረጉት። እሱ ግን ከትምህርቱም ሆነ ከሥራው ዓለም ይልቅ ውስጡ የሚመላለሰው የፈጠራ ሥራ ጉዳይ ነው።

በውስጡ ተዳፍኖ የቆየው የፈጠራ ሃሳብ አጋጣሚ ፈልጎ ከውስጡ አፈትልኮ የሚመጣበትን ጊዜ ሲጠብቅ ነበርና ጊዜው ደርሶ ከውጭ የተገዙ የተደረጉ እንጂ በሀገር ውስጥ የተሠሩ የማይመስሉ የፈጠራ ሥራዎችን ለመሥራት በቃ። ይህ የዛሬ የሳይንስና ቴክኖሎጂ አምዳችን ዛሬ ይዞት የመጣው የፈጠራ ባለሙያ አቶ ተሾመ ግርማ ይባላል።

አቶ ተሾመ፤ ገና ከልጅነቱ ጀምሮ የፈጠራ ክህሎት በውስጡ እንደነበር በሚሠራቸው የፈጠራ ሥራዎቹ ሲገልጻቸውና ለሚገጥሙት ችግሮች መፍትሔ ያላቸው ሃሳቦች እያመነጨ ወደ ፈጠራ እየቀየረ ሲሠራ ቆይቷል። በዚህም ጊዜ በውስጡ የነበረውን ተሰጥኦ በተለያዩ መንገዶች ሲያወጣ የተመለከቱ የአካባቢው ሰዎች ይደነቁበት እንደነበርም ያስታውሳል። በልጅነት እእምሮ ከማይረሳቸው መካከል የድንጋይ ወፍጮ ሠርቶ አፈር እና ጥራጥሬ በመጨመር እየፈጨ የአካባቢውን ሰዎች ሳይቀር ሲያስደንቅ የነበረበት ሁኔታ አንዱ ነው።

ወደ ትምህርት ቤት ገብቶ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቅቆ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርቱ ከገባ በኋላ ትምህርቱን አጠናቅቆ ወደ ሥራ ዓለም ቢሠማራም፣ የፈጠራ ሃሳቡን አውጥቶ ወደ ተግባር ለመቀየር እምብዛም ጥረት አላደረገም።

አሁን በንግድ ሥራ ተሠማርቶ እየሠራ ቢሆንም፣ በትርፍ ጊዜው በውስጡ ያለውን የፈጠራ ሃሳብ ወደ ተግባር ለመቀየር አቅዶ ተግባር ላይ ያውላል። የፈጠራ ሃሳቡን ወደ ተግባር መቀየር ቢችል ሀገር እንደሚጠቅምም ስለተረዳ በፈጠራ ሥራ ትኩረቱን ማድረግ ጀመረ።

አቶ ተሾመ፤ አሁን ከንግድ ሥራው በተጨማሪ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ የትምህርት ዘርፍ የማታ መርሃ ግብር ትምህርቱን እየተከታተለ ነው። በትርፍ ጊዜው የፈጠራ ሃሳቡን ወደ ተግባር በመቀየር በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ሦስት አይነት ብስክሌቶችን ሠርቷል።

ለብስክሌቶቹም የተለያየ ስያሜ አውጥቶላቸዋል። የመጀመሪያ ኤዲ -36 ቮልት የኤሌክትሪክ ስኩተር (AD-36V electric scooter)፣ ሁለተኛው ኢቲ- 72 ቮልት የኤሌክትሪክ ሳይክል (ET-72V electric Bike) እና ሦስተኛው ኢቲ-48 ቮልት ኤሌክትሪክ ትራይ ሳይክል ለአካል ጉዳተኞች (ET-48V electric Tricycle for Disablity) የሚል ስያሜ ተሠጥቷቸዋል።

አቶ ተሾመ እንዳብራራው፤ የመጀመሪያ የፈጠራ ሥራው የሆነው ኤዲ -36 ቮልት ኤሌክትሪክ ስኩተር የተሰኘው በኤሌክትሪክ የሚሠራ ብስክሌት ከተማው ውስጥ በደንብ ለመንቀሳቀስ እንዲችል ተደርጎ የተሠራ ነው። ባትሪው በጣም ትልቅና ሁለት ክፍል ያለው ነው። አንዴ ቻርጅ ተደርጎ በሰዓት ከ80 ኪሎሜትር በላይ መጓዝ ያስችላል። አንድ ባይስክል መያዝ ያለበትን ሁሉንም ነገር ያሟላ ከመሆኑም በላይ ለአፍሪካ ሀገሮች መንገዶች እንደሚች ተደርጎ ተሠርቷል። ባትሪው ቻርድ የሚደረግበት ፍጥነት እና ሳይክሉ ከመሬት በላይ ያለው ከፍታ እንዲጨምር ተደርጓል።

ሁለተኛው የፈጠራ ሥራው ኢቲ- 72 ቮልት ኤሌክትሪክ ሳይክል ደግሞ ከተማ ውስጥ ያሉ ሳይክሎችና ሞተር ሳይክሎችን ወደ ኤሌክትሪክ ሳይክልና ሞተር ሳይክል መቀየር እንደሚቻል ያመላከተ ነው። በጣም አቅም ያለው 70 ቦልት 20 አምፒር እስከ 1000 ዋት ያለው ሲሆን፣ በአንድ ጊዜ ቻርጅ ከ120 ኪሎ ሜትር በላይ መሄድ ያስችላል። ሦስት አይነት የፍጥነት ወሰኖች ያሉትም ነው፤ የመጀመሪያው የፍጥነት ወሰን በሰዓት እስከ 35 ኪሎ ሜትር ይነዳል። ሁለተኛው በሰዓት 55 ኪሎ ሜትር የሚነዳ ሲሆን፣ ሦስተኛው በሰዓት 85 ኪሎ ሜትር መሄድ ይችላል። ሁሉም አስፈላጊ ነገሮች

አቶ ተሾመ ግርማ

የተሟሉለትና ተፈትሾ የተረጋገጠ ነው።

ሦስተኛው ኢቲ-48 ቮልት ኤሌክትሪክ ትራይ ሳይክል ባለሶስት እግር ተደርጎ ለአካል ጉዳተኞች እንዲሆን የተሠራ ነው። በኤሌክትሪክ የሚሠራ ሲሆን፣ 48 ቦልት ይጠቀማል። የሀገሪቷን ነባራዊ ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ እንደ ልብ መውጣትና መግባት እንዲችል ታሳቢ ተደርጎ የተሠራ ሲሆን፣ ዲስክ ብሪክ የተሰኘ አዲስ ቴክኖሎጂም ተገጥሞለታል።

ይህን ትራይ ሳይክል ለመሥራት በብዛት የተጠቀምኩባቸው የሳይክል ቁሳቁስ ናቸው የሚለው ተሾመ፤ የሳይክል ቁሳቁስ በጣም ርካሽ ስለሆኑ በሀገራችን በቀላሉ የሚገኙ በመሆናቸው ምንም አይነት ችግር ቢያጋጥማቸው ከሳይክል ቤቶች ገዝቶ ለመቀየርና ለረጅም ጊዜ ለመጠቀም የሚያስችሉ ናቸው ሲል አብራርቷል።

ሌላው አዲስ የተጨመረው ደግሞ ከውጭ ከሚመጡ ሳይክሎች በተለየ መልኩ ሊትየም አየን የተሰኘ ባትሪ እየተገጠመ መሆኑ ነው። የዚህን ባትሪ ፓኬጅ እዚሁ በሀገር ውስጥ በማምረት እንደሚጠቀም ይገልጻል። ባትሪዎቹን ለመሥራት ከውጭ የሚመጣ ምንም አይነት ግብዓት እንደማያስፈልግ ተናግሮ፣ የላፕቶፕ ባትሪዎችን እንደገና ጥቅም ላይ በማዋል የባትሪዎቹን አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ እንደሚቻል አስታውቋል።

የፈጠራ ባለሙያው እንዳብራራው፤ ሊትየም አየንን መጠቀም ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው። የከተማ ባይስክሎች የሚጠቀሙት ሊድ አሲድ የተባለውን የቆየ ሞዴል ነው። ይህንን መጠቀማቸው ደግሞ የቆይታ ጊዜያቸው በጣም አጭር እንዲሆንና ቻርጅ ለማድረግ ብዙ ሰዓታት እንዲፈጁ ያደርጋል። ሙቀትን በራሳቸው መቆጣጠርም አይችሉም። በዚህ የተነሳም ባትሪዎቹ ብዙ ጥቅም ሳይሰጡ ቶሎ ይሞታሉ።

ሊትየም አየን የተገጠመላቸው ብስክሌቶች ባትሪዎቹ ግን ብዙ ይቆያሉ። እስከ ሦስት ዓመት የቆይታ ጊዜያቸው ይኖራቸዋል። ሙቀት የመቆጣጠር አቅማቸው ከፍተኛ ነው። ባትሪ የሚቆጣጠር ሲስተም የተገጠመላቸው ናቸው። አገልግሎታቸው ካበቃ በኋላ በቀላሉ ሊወገዱም ሆነ ሊጠገኑም ይችላሉ።

«ሊድ አሲድ ባትሪው ካቆመ ሙሉ ለሙሉ ማስወገድ እንጂ እንደገና መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል አይቻልም፤ ያለው አማራጭ መጣል ብቻ ነው። ሊትየም አየን ግን የተወሰኑ ሴሎቹ ከውስጡ ቢሞቱ እነዚያን በሌላ በመተካት አገልግሎቱ እንዲቀጥል ማድረግ ይቻላል» የሚለው አቶ ተሾመ፤ ይህም ሳይክሎቹን ከሌሎች ከውጭ ከሚገቡ ሳይክሎች የተለየ እንዲሆን እንዳደረገው ያስረዳል።

የመጀመሪያ የፈጠራ ሥራው የሆነውን ኤዲ -36 ቮልቴጅ ኤሌክትሪክ ስኩተር ያለበትን ምክንያት ስያስረዳ ኤዲ/ AD/ በሚለው እናቱ ለማስታወስ፣ ከእናቱ ሙሉ ስም መጀመሪያ ፊደል ወስዶ መሰየሙንና 36V የሚለው ቮልቴጁን የሚገልጽ እንደሆነ ያብራራል።

ሁለተኛው ET-72V ኢቲ ኢትዮጵያ ፤ 72V ደግሞ ቮልቴጁን የሚገልጽ መሆኑን ጠቅሶ፤ ሦስተኛው ET-48V ኢቲ ኢትዮጵያ 48V የቮልቴጁን መጠን እንደሚገልጽ ያስረዳል።

የመጀመሪያ የፈጠራ ሥራ አይነት ኤሌክትሪክ ስኩተር ሳይክሎች ወደ ሀገሪቱ ብዙም አልገቡም፤ የሉም ማለት ይቻላል ሲል አቶ ተሾመ ተናግሯል። የኮሪደር ልማቱ እነዚህን ነገሮች ያበረታታል በሚል ሃሳብ ሳይክሉን እንደሥራው ይገልጻል።

ስለሁለተኛው የፈጠራ ሥራው ሲያብራራም ሁለተኛው የፈጠራ ሥራው ከውጭ ከሚመጡት ባይስክሎች እንደሚለይ ተናግሮ፣ የዚህ አንዱ ምክንያት የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ከግንዛቤው ውስጥ በማስገባት የተሠራ በመሆኑ ነው ይላል። እንደ ሀገር እነደዚህ አይነቶቹ ብስክሌቶች በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ከምናስመጣ የተወሰኑ ነገሮች ብቻ በማስመጣት ለምን ሀገር ውስጥ መሥራትና ማምረት አንችልም በሚል ሃሳብ ለመሥራት እንደቻለ ይናገራል።

ሦስተኛውን የፈጠራ ሥራ ለመሥራት የተነሳሳው ካዛንቺስ አካባቢ አንድ አካል ጉዳተኛ የሚጠቀምበት ዊልቸር ተመልክቶ መሆኑን ያስታውሳል። ከየት አመጣህ ? በስንት ብር ገዛኸው ? ብሎ ሲጠይቀው አካል ጉዳተኛው የሰጠው ምላሽ ልቡን እንደነካው አቶ ተሾመ ይናገራል። አካል ጉዳተኛው በእኛ ሀገር አቅም መግዛት እንደማይቻል፣ በግብረ ሰናይ ድርጅት አማካኝነት ያገኘው መሆኑን ሲነግረው ለምን እኛ እንሠራውም በሚል ቁጭት ተነስቶ አካል ጉዳተኞች ለመርዳት እንደሠራው አስታውቋል።

አቶ ተሾመ እንደሚለው፤ እነዚህ የፈጠራ ውጤቶች በዋጋም ቢሆን ከውጭ ከሚገቡት ጋር የሚነጻጸሩ አይደሉም፤ ከውጭ የሚገቡት በጣም ውድ ናቸው። በሀገር ውስጥ የሚመረቱት ግን ብዙ ቁሳቁሳቸው በቀላሉ ይገኛል፤ መልሶ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳቁስ በብዛት ይገኛሉ። በዚህ የተነሳ ዋጋቸው ተመጣጣኝ ነው። አሁን ባሉበት ያላቸው ዋጋና ወደ ማኑፋክቸሪንግ ተገብቶ በብዛት ሲመረቱ በራሱ ያላቸው ዋጋ ልዩነት ያመጣል። የፈጠራ ሥራዎቹ ግሪን ቴክኖሎጂ የሚባሉም ናቸው፤ ይህን ያሰኛቸው ዋና ምክንያትም የአካባቢን ብክለት የሚቀንሱ መሆናቸው ነው።

አቶ ተሾመ በፈጠራ ሥራ በትኩረት መሥራት ከጀመረ ሁለት ዓመታት ያህል ያስቆጠረ ቢሆንም፣ ሥራዎቹን ለመጀመሪያ ጊዜ በሳይንስ ሙዚየም በተዘጋጀው ዓለም አቀፍና የሀገር በቀል ቴክኖሎጂ አውደ ርዕይ አቅርቧል። በግሉ በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ እየሠራ ቢሆንም፣ በትርፍ ጊዜው ደግሞ የፈጠራ ሥራዎችን ይሠራል። በተጨማሪ በማታው መርሃ ግብር እየተማረ ያለው ኤሌክትሪካል እና ኮምፒዩተር ኢንጂነሪንግ ትምህርት የፈጠራ ሥራዎች ለመሥራት ረድቶታል። በኤሌክትሪካልና ኮምፒዩተር ኢንጂነሪንግ ያገኘውን እውቀትም ከመካኒካል ጋር አያይዞ ከመጀመሪያ አንስቶ እስከ መጨረሻ ያለውን ሥራውን ለመሥራት አስችሎታል።

«የፈጠራ ሥራዎቹን ከሁለት ነገሮች በስተቀር ከዲዛይን ጀምሮ ኤሌክትሪኩን መገጣጠምና እስከ ቅብ ድረስ ያሉትን ሁሉም ሥራዎች በእኛ ነው የሚሠሩት። እነዚህን የተወሰኑ የተባሉትን ነገሮች በሀገር ውስጥ ለመሥራት ከባድ ስለሆኑ ከውጭ እናስመጣለን። ሀብ ሞተር እና ኮንትሮለር ብቻ ከውጭ እናስመጣለን» ሲል አብራርቷል።

«የፈጠራ ሥራዎች ለመሥራት ለረጅም ጊዜ ብዙ ማሰብ፣ ማሰላሰልና ማቀድን ይጠይቃሉ» ሲል አቶ ተሾመ ይገልጻል፤ የፈጠራ ሥራዎቹን በትርፍ ጊዜው እንደሚሰራቸው ጠቅሶ፣ ጊዜውን ሁሉንም ሥራ በማይጎዳ መልኩ ከፋፍሎ እንደሚጠቀም ይገልጻል። « ሁሉንም ሰዓቴን በአግባቡ ከፋፍዬ እጠቀማለሁ። ስፖርት ከመሥራት ጀምሮ ልጆቼን ትምህርት ቤት ማድረስ፣ የቢሮ ሥራዬን መሥራት እና የማታ ትምህርቴን መከታተሌ እንዳለ ሆኖ የሚተርፉኝ ሽርፍራፊ ሰዓቶች ደግሞ የፈጠራ ሃሳብ ማሰላሰልና ዲዛይን ማድረግ ላይ አውላለሁ» ይላል። እንደ ዩቲዩብ ያሉ ሶሻል ሚዲያዎችን ያሉትን መጠቀሙ የምፈልጋቸው ዲዛይኖች ለመሥራትና እውቀት ለማግኘት እንደረዱትም ይናገራል።

አቶ ተሾመ እነዚህን ሦስት የፈጠራ ሥራዎች ሲሠራ ቅድሚያ የሰጠው ለሥራው እንጂ የባለቤትነት መብትን ለማስጠበቅ እምብዛም እንዳልሄደበት አመልክቷል። አሁን የባለቤትነት መብት ለማግኘት የፈጠራ ሥራዎቹን አእምሯዊ ንብረት ጽህፈት ለመውሰድ በሂደት ላይ መሆኑን አስታውቋል።

የባለቤትነት መብቱን ካገኘ በኋላ ወደ ኢንዱስትሪ ደረጃ ለመግባት ይፈልጋል። ለዚህ ደግሞ እንደ መሥሪያ ቦታ እና ካፒታል የመሳሰሉት ነገሮች የግድ ናቸው። ከውጭ ለምናስመጣቸው እቃዎች ከታክስ ጋር የተያያዙ ነገሮች ላይ በተወሰነ መልኩም ቢሆን አስተያየት ቢደረግ ወደ ሥራ ገብቶ ማምረት እንደሚችል ተናግሯል።

በሀገሪቱ በርካታ የፈጠራ ሃሳብ ያላቸው ሰዎች እውቀቱም እንዳላቸው ገልጾ፣ የፈጠራ ሃሳቡን ወደ ተግባር ለመለወጥ ብዙ እንደማይቸገሩ አስታውቋል። አብዛኛውን ጊዜ ችግር የሚሆንባቸው የግብዓት አቅርቦት ነው ሲል ጠቁሞ፣ በሀገሩ ውስጥ የሌሉ ተራ የሚባሉ ቁሶችን ከውጭ ለማስመጣት ችግር ሊገጥም እንደሚችል ያስረዳል።

በተለይ ወደ ፈጠራ ሥራ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚገቡ ሁሉ ተስፋ መቆረጥ እንደሌለባቸው ገልጾ፣ በአእምሮአቸው የሚያሰላስሉትን ሃሳብ አውጥተው ወደ ተግባር መቀየር እንዳለባቸው አስገንዝቧል። «እኔ ለረጅም ዓመታት ብዙ የፈጠራ ሥራዎችን በሃሳቤ አውጥቼ አውርጄለሁ። ተግባር ላይ እንዳላውል የሚይዙኝ ነገሮች ነበሩ» ሲል አብራርቶ፣ የፈጠራ ሥራ ጀማሪዎች ምንም ይሁን ምንም ያሰቡትን ነገር ከውስጣቸው አውጥተው በተግባር ሊያውሉ እንደሚገባ አስገንዝቧል። «ፈጠራ በተግባር ካልተደገፈ በሃሳብ ብቻ ከንቱ ነው፤ አየር ላይ ነው የሚቀረው። እኔ ካገኘሁት ተሞክሮ የተገነዘብኩት ሃሳብ ተግባር ላይ ሲውል ሁሉንም ሰው መሳብ እንደሚችል ነው» ሲል አመላክቷል ።

ፖለቲካና ወቅታዊ

ወቅታዊ ትንታኔ

ለኢኮኖሚው እድገት -የመንግሥት እና የግሉ ዘርፍ ትብብር እስከምን ድረስ ነው ?

አስቴር ኤልያስ

ኢትዮጵያ ከወራት በፊት የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ማድረጓ እሙን ነው። ማሻሻያ ለማድረጓ ዋና ምክንያት ከለውጡ አስቀድሞ የነበረው የማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ማራመድ የማያስችል በመሆኑ ነው። በተለይም ኢትዮጵያን ፈትኗት የቆየው የውጭ ምንዛሬ እጥረትና የግሉ ዘርፍ በሚፈልገው ልክ ብድር ማግኘት አለመቻል ማሻሻያው አስፈላጊ እንዲሆን ማድረጉን በወቅቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ማሞ ምህረቱ መናገራቸው ይታወሳል። ሀገር በቀል ኢኮኖሚ ሪፎርም መንደፍ የማክሮ ኢኮኖሚ ውድቀትን ለመታደግ የሚያስችል እንደሆነም ማስረዳታቸው ይታወቃል።

ከሳምንታት በፊት በፕላንና ልማት ሚኒስቴር አስተባባሪነት« የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ትናንት የነበረው፣ ዛሬ ያለውና ወደፊት ስላለው ሁኔታ» ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት የተካሄደ መሆኑ ይታወቃል። በወቅቱ ከአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ እስከ ደርግ እና የኢህአዴግ መንግሥት ድረስ ስላለው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዳሰሳ ተደርጎበታል። በአሁኑ ወቅት እየተተገበረ ስላለው የኢኮኖሚ አተገባበር በስፋት ውይይት ተካሂዶበታል።

በውይይቱ ወቅትም በተለይም ከግሉ ዘርፍ የተለያዩ ጥያቄዎች የተነሱ ሲሆን፣ ትኩረት ያደረጉትም ሥልጡን የሰው ኃይል አስፈላጊነት ላይ፣ በሚጣለው ታክስና ቫት ጉዳይ ላይ፣ የውጭ ባለሀብት እንደሚበረታታው ሁሉ የሀገር ውስጥ ባለሀብቱን ማበረታት ላይ ምን የታሰበ ነገር አለ የሚሉት ጥቂቶቹ ሲሆኑ የሚመለከታቸውም አካላት በተነሱት ነጥቦች ላይ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ አቶ ማሞ ምህረቱ እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ በኢኮኖሚው መስክ ያደረገችው ሪፎርም እያሳየ ያለው ውጤት በጣም መልካም የሚባል ነው፤ ምክንያቱም ሪፎርሙ በሚቀረጽበትና ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ ዋና ጉዳይ ምንድን ነው ከተባለ እንደ ግሉ ዘርፍ ያሉ አምራችን ለማበረታታት እንዲሁም የወጪ ንግድን ለማሳደግ ታስቦ ነው። ከዚህ በፊት የነበረው አሠራር በሕጋዊ መልኩ ኤክስፖርት የሚያደርጉ አካላትን በእጅጉ የሚጎዳ ነው።

ጥንቅቅ ያለ ሥራ እንዲሆን ለማድረግ የሚቀሩ ነገሮች እንዳሉ እናውቃለን ያሉት የባንኩ ገዥው፣ በእኛ እምነት የተነሱ ዓይነት ችግሮች በሂደት እየተፈቱ የሚሄዱ ሲሆን፣ ችግሮችን እየለየንና እየፈታን ለመሔድ እንሠራለን ብለዋል።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ የተረጋጋ የውጭ ምንዛሬ ሥርዓት ውስጥ ስለገባን የውጪ ምንዛሬ አቅርቦት ሊሰፋ ይገባል፤ ይህን ለማድረግ የተለያዩ ሥራዎች መሠራት አለባቸው። ከዚህ ውስጥ አንዱ ከአሁን በፊት ከነበረው በተሻለ ሪሜታንስን ማበረታታት ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ ተጨማሪ ሥራዎችን መሥራት ይጠበቃል።

እንደግሉ ዘርፍ ኤክስፖርት የሚያደርግ ድርጅት ደግሞ ያገኘውን የውጭ ምንዛሬ ግኝት ካለምንም ችግር ሳይቀንስና ሳይጨምር ለባንኮቹ መስጠት እንዳለበት የተናገሩት ገዥው፣ ባንኮችም፣ ኤክስፖርተሮችም፣ የግል ዘርፉም በዚህ ዙሪያ በትብብር መሥራት አለበት ብለዋል። የመሰባሰባችን ዋና ዓላማም በትብብር በመሥራት የኢኮኖሚ ችግሮቻችንን በጋራ ለመፍታት እንደሆነ ተናግረዋል።

ለባንኮች ማስታወቅ የምፈልገው ነገር የውጭ ምንዛሬው ሥርዓት አያያዝ እየተረጋጋ ስለሆነ ባንኮች በተለየ ትኩረት የውጭ ምንዛሬ የማሰባሰብ ሥራ ላይ ሊሰሩ ይገባል። በተለይ ከውጭ የሚላክ ገንዘብን በተመለከተ በስፋት መሥራት አለባችሁ ብዬ አስባለሁ ሲሉ አቶ ማሞ አሳስበዋል። ሰዎች የውጭ ምንዛሬ ማግኘት የሚችሉ ከሆነ ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ ይረዳል። ስለዚህ በዚህ አቅጣጫ መሥራት ተገቢ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

የብሔራዊ ባንክ ገዥው እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ባለፉት ስድስት ዓመታት ብዙ የተሞከሩ ሥራዎች አሉ። እንዲህ ሲባል ቀደም ባሉ ዓመታት የተሞከሩ ሥራዎች ሁሉ ምንም ዋጋ የላቸውም ማለት አይደለም። ከዚህ በፊት የነበሩት መንግሥታት በገባቸው ልክ በቅን ልቦና ሀገራቸውን ወደፊት ለማሳደግ ሰርተዋል። ከሰሩትም ሥራ የሚወሰድ ነገር አለ።

የኢኮኖሚ እድገት ስንል ተከታታይነትና የተረጋጋ ኢኮኖሚ መፍጠርን፣ አንድነትንና በጋራ መሥራትን፣ ሰላማችንን በሚገባ ማረጋገጥን ይጠይቃል

ከዚህ በፊት በነበረው አሠራር ወጥ በሆነ መልኩ ሁሉንም ነገር መንግሥት ብቻ ይሥራው የሚል ነበር፤ ይህ አካሔድ ትክክል አይደለም፤ በደርግ አይተነዋል። መንግሥት ብቻውን ልማት ሊያመጣ አይችልም። በሌላ በኩል የግሉ ዘርፍ ብቻ ሥራውን ይሥራ ሊባልም አይችልም። ምክንያቱም በእኛ ሀገር ያለው የግሉ ዘርፍ እያደገ ቢሄድም ብቻውን ግን የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ሊሸከም አይችልም። ስለዚህ ዋናው ቁልፉ ነገር ምንድን ነው ከተባለ ሀገራችንን ወደፊት ለማራመድ ከፈለግን ገበያን በሚደግፍ መንግሥት፣ የግል ዘርፉን በሚደግፍ መንግሥትና በግል ዘርፉ ትብብር ሀገራችንን ማሳደግ ነው። ዋና ነጥቡ የትብብርና የጋራ መንፈስ መኖር መቻል አለበት ይላሉ።

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታው እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በግሉ ዘርፍ የተነሱ ሃሳቦች ተገቢ ናቸው ይላሉ። ልክ እንደ ብሔራዊ ባንክ ገዥው ሁሉ እርሳቸውም፤ የሀገር ልማት የጋራ ሥራ መሆኑ እሙን ነው ይላሉ። አከለውም እኛ እድለኞች ነን ብዬ አስባለሁ። የኢትዮጵያን ለዘመናት ቆየ የኢኮኖሚ መሻት ለማሳካት የሚችልበት የተሟለ እይታ እየመጣ ነው። የተሟለ እይታ ሲባል የመንግሥት ቁርጠኝነት፣ የሕዝቡ መነሳሳት፣ የግሉ ዘርፍ ለአጋርነት መቆም እንዲሁም ከየት ተነስተን ምን እንደምንፈልግ ግልጽ የሆነ ነገር ይዘናል ማለት ነው። ይላሉ።

በየትኛውም ሀገር ተሞክሮ ወስዳችሁ ብታዩት ሀገር የምትበለጽገው አንድ ትውልድ ጨክኖ በሚሠራ ሥራ ነው። አንድ ትውልድ ጥርሱን ነክሶ አሻጋሪ የሆነ ሥራ መሥራት አለበት። የኢትዮጵያ ሕልም ምንድን ነው በጋራ መሄድ የምንችለው የት ነው። እስካሁንስ ሳይሳካ የቀረው ለምንድን ነው የሚለውን መለየት ያስፈልጋል። በቀጣይም ይህ ትውልድ የብልፅግና ጉዞውን ያሳካል የሚለው ላይ ርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

የአምራች ዘርፉን ማገዝ ተብሎ ለተነሳው ጥያቄ የአምራች ዘርፉን ጠጋ ብሎ በመምራትና በማገዝ ረገድ ባለፉት አምስትና ስድስት ዓመታት የተሔደበትን ርቀት ማየቱ መልካም እንደሆነ ጠቅሰው፤ ይህም ለቀጣይ ሥራ አጋዥ ነው ብለዋል። መንግሥት ብዝሀ ዘርፍ ላይ ትልቅ ሥራ እየሠራ እንደሆነም አስታውሰዋል። ግብርና ላይ የመጣው የሚገርም ሥራ ነው፤ መንግሥት ማዕድን፣ ቱሪዝምና ሌሎችን ጨምሮ ብዝሀ ዘርፍ ላይ በተከታታይ ለመሥራት ሞክሯል።

በዕለቱ የኢትዮጵያን የትናንቱን፣ የዛሬውንና የነገውን ኢኮኖሚ ምን እንደሚመስል ያቀረቡት የፕላንና ልማት ሚኒስትሯ ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በታዳሚያኑ የተነሱ ጥያቄዎች እንደየዘርፉን የሚወሰዱና እንዴት የፖሊሲ ግብዓት ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚታዩ ይሆናሉ ብለዋል።

ፍጹም (ዶ/ር) ልክ እንደ እዮብ (ዶ/ር) ሁሉ ሀገርን ለማሻገር አንድ ትውልድ የግድ ዋጋ መክፈል አለበት ይላሉ። እነዚያ የሚያሻግሩ ትውልዶች ቁርጥ አቋም የሚወስዱና ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ የሆኑ እንደሆነም አስረድተዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ያደጉ ሀገሮችን ታሪክ ስናጤን ጥቂት የማይባሉቱ ያደጉት አንድ ትውልድ በከፈለው ዋጋ መሆኑን ያነሱት ሚኒስትሯ፣ እንዲያም ሆኖ የሁሉም ልምድ አንድ ዓይነት ነው ማለት እንደማይቻል አመልክተዋል። የሚያሳየን ነገር ቢኖር አንደ ትውልድ ዋጋ መክፈል እንዳለብን ነው። ይህ ዋጋ የከፈለ ትውልድ፣ ሁሉ ነገር አልጋ በአልጋ ሆኖለት ሳይሆን ለልጆቹ የተሻለ ሀገር ለመሥራት ዋጋ መክፈል ስላለበት የሚያደርገው ሲሉ ገልጸዋል።

ስለሆነም የሀገር ውስጥ የግሉ ዘርፍ፣ ሀገሩ ኢትዮጵያ ስለሆነች ከውጭ ከሚመጣው ይልቅ በእኔነት መንፈስ አንድ ሆኖ ተናብቦ የረጅም ጊዜ ሕልማችንን እንዲጋራ ነው ፍላጎታችን ይላሉ። ዋና ዓላማው እኛ ይህን ዋጋ ለመክፈል የተመረጥን ትውልዶች መሆናችንን መረዳት ነው። ስለዚህም ዋጋ ከፍለን ከፊት ለፊታችን የምናየውን ግብ እና አጓጊ ሕልም እንድናሳካ አብረን እንሁን ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

እንደ አቶ ማሞ ገለጻ፤ መንግሥት ብቻውን የኢትዮጵያን ችግር ሊፈታ አይችልም። ስለዚህ የግሉ ዘርፍ የራሱን ሚና መወጣት መቻል አለበት። የሁለቱ ትብብር ሀገሪቱን ወደፊት የሚያስኬዳት ይሆናል። ለዚህ ደግሞ ጥንካሬን ይፈልጋል። በተቻለ መጠን መንግሥት የግሉን ዘርፍ መደገፍ ይጠበቅበታል። የግል ዘርፉ ሀብት እንዲፈጥር ሊገፋፉ ይገባል። የግሉ ዘርፉ የተሻለ ሀብት አፍርቶ፣ የሥራ እድል ፈጥሮ የተሻለ የውጭ ምንዛሬ አስገኝቶ ሀገሪቷን ወደፊት ሊያሳድግ ይገባል።

ሌላው ፍጹም (ዶ/ር) እንደጠቀሱት፤ በተቻለ መጠን መንግሥት የረጅም ጊዜ እይታ ያለው መሆን አለበት። ይህን ለማድረግ ሁለት ቁልፍ ነገሮች አሉ። አንደኛ የግሉ ዘርፍ እንዳነሱት ሁሉ የረጅም ጊዜ የሰብዓዊ ልማት ላይ መሥራት ያስፈልጋል። ለምን ቢባል የለሙ ሀገሮችን ካልለሙ ሀገሮች የሚለየው ትልቁ ነገር ምንድን ነው ከተባለ ቴክኖሎጂ ነው። ቴክኖሎጂ ደግሞ በሰው አዕምሮ ያለ ነገር ነው። የረጅም ጊዜ እይታ ማለት በሰው ልማት ላይ ኢንቨስት ማድረግ፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ ወደፊት የሚያስኬደን የጋራ የሕዝብ ኢንቨስትመንት መሠረተ ልማት ላይ የሚተኩር መሆን አለበት።

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ መንግሥት ታዳሽ ኃይል ላይ ኢንቨስት እያደረገ ነው። ይህ በዋናነት ዓላማው ምንድን ነው ከተባለ የኢትዮጵያ እድገትና የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ልማት ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲጓዝ ስለታሰበ ነው።

የሀገራችንን ልማት ለማረጋገጥ ከፈለግን የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ አስፈላጊ ነው። ይህ መሠረታዊ ነው። የውጭ ምንዛሬ አስተዳደሩ፣ የገንዘብ ፖሊሲ አስተዳደሩ፣ የፊስካል አስተዳደሩ፣ የፋይናንስ ሴክተር አስተዳደሩ በተቻለ መጠን የተረጋጋ መሆን አለበት። ይህ ስኬታማ የሚሆነው በትብብር መሥራት ሲቻል ነውና አብረን እንሥራ ሲሉ ጥሪ ያቀርባሉ። ለመንግሥት ብቻ የሚተው ሥራ እንደሌለም ጠቅሰው፤ ሥራውን በጋራ እንሥራ ሲሉ ያበረታታሉ።

ፍጹም (ዶ/ር)፣ የባንክ ገዥውን ሐሳብ ሲያጠናክሩ እንዳሉት፤ መንግሥት የሚያወራው ስለአምስት ዓመት ርዕይ ሳይሆን የረጅም ጊዜ እና ለትውልድ ስለሚሻገር እይታ ነው። ይህን ሕልም የግሉ ዘርፍም ሆነ ሁሉም እንዲጋራ ይፈለጋል። የአጭር ጊዜ ፈተናዎችን እንደምንፈታው ሁሉ የረጅም ጊዜ ሕልማችን እውን እንዲሆን ከወዲሁ አካሔዳችንን ማስተካከል ይኖርብናል።

ግብርና ላይ ትኩረት የምናደርገው ለሌሎቹ ዘርፎች ወሳኝ በመሆኑ ነው። በሌላ በኩል የሰው ሀብት ልማት ላይ መሥራት አለብን፤ ርካሽ የሰው ኃይል ሳይሆን ተወዳዳሪ የሆነ የሰው ኃይል ላይ እንሠራለን ሲሉ ፍጹም (ዶ/ር) ተናግረዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው እዮብ (ዶ/ር)፣ ታክስን በተመለከተ ሲናገሩ፤ ሁሉም የራሱ ሴክተር ታክስ እንዳይጣልበት ፈላጊ መሆኑ ሲሆን፣ ታክስ ካልሰበሰብን ደግሞ የምናሰበውን ሀገራዊ ለውጥ ልናመጣ አንችልም ሲሉ ያስረዳሉ። ስለዚህም ሚዛን መጠበቅ የግድ ነው ይላሉ።

በተዘዋዋሪ መንግሥት በተለያዩ አቅጣጫዎች ከፍተኛ ድጎማ እያደረገ ነው። ከተማሪ ምገባ ጀምሮ በሴፍትኔት ብዙዎቹን እየመገብን ነው። ዘይት ደጉመን እያስገባን ነው። በጣም ደሃ ተኮር የሆነ መንግሥት ነው። በጥቅሉ አሁንም ቢሆን ድጋፍ የሚፈልጉትን ዘርፎች ለይተን የምንደግፍ ይሆናል ብለዋል።

አሁን ሪፎርም ጨርሰናል። ስለሆነም አሁን የአዝመራ ጊዜ ነው። የዚህን ሪፎርም ውጤት በዘርፎች የምናይበት፣ ሀገር ሽግግር ላይ መሆኗን የምናይበት እንዲሁም በአጠቃላይ ለኢትዮጵያውንና ለኢትዮጵያ ያስቀመጥንላት ግብ የሚሳካ መሆኑን የምናይበት ጊዜ ነው። ትልቁን ሥራ አመራር የሚቀጥል ሲሆን፣ ታክስ መክፈል፣ የግሉን ዘርፍ ማበረታታት፣ ባንኩሩ በአግባቡ የጋራ የፋይናንስ ሥርዓት ውስጥ እንዲገባ ማድረግ፣ ይህን እየፈጠርን መሔድ ይጠበቅብናል። የኢትዮጵያ ብልፅግና እነዚህን መሰል ድልድዮች ይፈልጋል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አህመድ ሺዴ የዕለቱ ውይይት ዋና ዓላማ፤ ዘመናዊ ኢኮኖሚ መገንባት ነው። በዚህም በሁሉም ዘርፎች ተከታታይ የሆነ ውጤት መምጣቱን ለማረጋገጥ የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ እድገትን ማረጋገጥ ነው። በተለይ የረጅም ጊዜ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን የተሟላ ማክሮ ኢኮኖሚ ሪፎርሙን ተከታታይነት እንዲኖረው ማድረግ ይጠይቃል።

ስለሆነም ዋናው ነገር ተከታታይነት ያለው፣ ዘላቂነት ያለው በቴክኖሎጂ እድገት የታገዘ፣ ዘርፈ ብዙ እድገት ማረጋገጥ ነው። ግብርና ላይ ብቻ ሳይሆን እኛ ትኩረት ማድረግ ያለብን ሁሉም ዘርፍ ላይ ነው ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ የኢኮኖሚ ሚና ያላቸው ኃይሎችን በጠቅላላ በተሟላ መልኩ ምርታማ እንዲሆኑ ማስቻል ነው። የግሉን ዘርፍ በሚገባ ማብቃት፣ የሕዝቡን የተደራጀ ተሳትፎ ማጠናከር፣ የመንግሥት ተቋማት ብቃት ያለው አገልግሎትና ሀብትን ወደ ንብረት የመቀየር ጉዳይ በሚገባ እንዲያሳኩ ማድረግ ነው። ሕዝቡን በአግባቡ በማስተዳደር ሰላምን አረጋግጦና አጠናክሮ መሄድ ነው።

ስለዚህ ጠንካራና ዘላቂ ተቋማት ያለው ሀገረ መንግሥት መገንባት የሚቻለው መሠረት ልማት ላይ በብቃትና በተከታታይነት ኢንቨስት ማድረግ ሲቻል ጭምር ነው። ዘርፈ ብዙ በሆነ መልኩ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የመደገፍና የማብቃት፣ የውጭ ባለሀብቶች ወደ ኢኮኖሚያችን ገብተው እንዲያሳድጉ ማድረግም የሚጠበቅ ነው ብለዋል።

ይህን ለማድረግ የቁጠባ መጠንን ማሳደግ ያስፈልጋል። ከውጭ የሚላከውን ገንዘብና የኤክስፖርትን መጠን በኢኮኖሚው ውስጥ ማሳደግም ወሳኝ ነው። ሁሉም ዘርፎች ለገቢም ለኤክስፖርትም በከፍተኛ ደረጃ እንዲያመርቱ ማድረግ ላይ ትኩረት ተደርጓል። ቱሪዝም፣ ግብርና፣ ኢንዱስትሪ፣ አገልግሎት እንዲሁም ዲጂታል ኢኮኖሚ ላይ ትኩረት የተደረገው ለዚያ ነው። ስለዚህ ዘርፈ ብዙ እድገትን ማረጋገጥ፣ ባለብዙ ተዋናዮችን ሚና በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ፣ ይህም ዘላቂ እንዲሆን ማድረግ፣ የረጅም ጊዜ እይታ ያለው አጠቃላይ አካሔድ ነው ያለን ሲሉ አብራርተዋል።

ለዚህም ነው የ30 የ50 ዓመት እያልን በረጅም ጊዜ ትልም እየተንቀሳቀስን ያለነው ያሉት አቶ አሕመድ፣ ይህ ደግሞ እንደተባለው የትውልድን ቁርጠኝነት የሚጠይቅ ነው ብለዋል። የኢኮኖሚ እድገት ስንል ተከታታይነትና የተረጋጋ ኢኮኖሚ መፍጠርን፣ አንድነትንና በጋራ መሥራትን፣ ሰላማችንን በሚገባ ማረጋገጥን ይጠይቃል። በተለይ ደግሞ ሁሉም ዘርፎች በኢኮኖሚ ላይ ያላቸው ተሳትፎ በሚገባ ማሳደግን የሚጠይቅ መሆኑን አመልክተዋል።

የግሉ ዘርፍ ዋነኛው የልማት ሞተር ነው። መንግሥት ያለው ሚና የማስተባበርና ምቹ ሁኔታን የመፍጠር ብሎም የመምራት ነው። ስለዚህ ሁሉም ዘርፎች የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ የተቀመጠው የረጅም ጊዜ እቅድ ነው። ይህ ደግሞ የጋራ ሥራን ይጠይቃል። ሀገራችን የበለጸገች እንድትሆን በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካና በማኅበራዊ ዘርፍም ጠንካራ ሆና እንድትሔድ የሚሰራው ሥራ ተጠናክሮ የሚሄድ ይሆናል ሲሉ ገልጸዋል።

ማህበራዊ

ሴቶች

መጥፎን አጋጣሚ ወደ መልካም የቀየሩ እናት

አመስወርቅ ከበደ

ጥሮ ግሮ ማደርን ባሕል ያደረጉ፣ እድሜ ያልገደባቸው ጠንካራ እናት ናቸው። አርብቶ አደርነት እንኳን እንደሳቸው ከተማ ተወልዶ ላደገ ሰው ይቅርና እድገቱን ገጠር ላደረገም ትልቅ ጥረት እና ልፋትን ይጠይቃል። እሳቸው ግን የከተማን ሰው ሥራ አይችልም ያለው ማነው ብለው የተነሱ ቆራጥ ናቸው። ሁሉንም በልኩ በጥበብና በብርታት ይዘው ውጤታማ መሆን ችለዋል።

ከተሜነታቸውም የከብት ሳር ከማጨድ አንስቶ ሌሎች ተያያዥ ሥራዎችን ለመከወን አላገዳቸውም። ምክንያቱም ሥራውን የጀመሩት ዓላማ ይዘው ነው። የሥራቸው ትልቁ ዓላማ በሞት የተለያቸውን የአብራካቸውን ክፋይ ማስታወስ ነው። አለፍ ሲልም አንገት አስደፊ ከሆነው ድህነት ማምለጫ መፍትሔው ሥራ መሆኑን በመገንዘባቸው ነው።

በአርአያነታቸው የመረጥናቸው ብርቱ ሴት ወይዘሮ ወይንሸት ጥላሁን ይባላሉ። ወይዘሮዋ የሚኖሩት እንጦጦ አካባቢ ሲሆን፤ ባለትዳርና የአራት ልጆች እናት ናቸው። የ65 ዓመት እድሜ ባለፀጋ የሆኑት ወይዘሮ ትውልድና እድገታቸው አዲስ አበባ ከተማ ቀጨኔ መድኃኒዓለም አካባቢ እንደነበር አጫውተውናል።

ትምህርት የማግኘት አማራጭ ከገጠር ይልቅ በከተማ አካባቢ የተሻለ እንደሆነ ቢታመንም፤ እሳቸው ግን ከደሃ ቤተሰብ በመወለዳቸው እና በወቅቱ ማህበረሰቡ ለሴት ልጅ ትምህርት ካለው አመለካከት የተነሳ መደበኛ ትምህርት የማግኘት እድል አልገጠማቸውም።

“የተማርኩት መሠረተ ትምህርት ብቻ ነው። ቤተሰቦቼ እኔን ለማስተማር አቅም ከማጣታቸው ሌላ ቀደም ሲል ሴት ልጅ ትምህርት እንድትማር ያለው አመለካከት እስከዚህም ነው። ከዚህ የተነሳ ከልጅነት እስከ እውቀት እድሜዬን በልፋት ነው ያሳለፍኩት።” ይላሉ።

የተለያዩ ሥራዎች በመሥራት እራሳቸውን ሲያስተዳድሩ ነበር ከባለቤታቸው ጋር ተገናኝተው ትዳር የመሠረቱት። በትዳራቸው አራት ልጆችን ያፈሩ ሲሆን፤ አንደኛው ልጃቸው ወታደር ቤት ግዳጅ ላይ እያለ ነው የተሰዋው።

ወይዘሮ ወይንሸት ወደ ከተማ ግብርና ከመግባታቸው በፊት ከሚያረቧቸው ጥቂት በጎች ውጭ፤ በባለቤታቸው ደሞዝ ነበር የሚተዳደሩት። አጋጣሚ ሆኖ ልጃቸው በግዳጅ ላይ ስለሞተ በተሰጣቸው የካሳ ክፍያ ላም ገዝተው ወደ ከብት ርባታ ሥራ ገቡ።

“አጋጣሚ ልጄ ወደ ውትድርና ገብቶ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ግዳጅ ላይ ስለሞተ ዳረጎት ተሰጠኝና ገንዘቡን ሳላጠፋ፤ አንድም የልጄ ማስታወሻ እንዲሆነኝ በማለት ሥራ ፈጠርኩበት።” ሲሉ ይናገራሉ።

የካሳ ክፍያውን የተቀበሉት ልጃቸው ከሞተ ከሶስት ዓመት በኋላ እንደነበር በመግለጽ፤ ታናናሽ ልጆች ስለነበሯቸው እነሱን እያሳደጉ፤ አንድ የህበሻ ላም በአራት ሺህ ብር ገዝተው ነው ሥራውን የጀመሩት። ያች ላም እየወለደች ወደ ለውጥ መንገድ እንዲገቡ ምክንያት ሆነች።

ከዛ ቀጥለው ዝርያዋ የተሻሻለ ጥጃ ገዝተው አሳደጉና ጥጃዋ ስታድግ አምስት ሴት ላሞች ወለደች። መጀመሪያ የገዟትን ላም ሸጠው ዝርያቸው የተሻሻሉ ላሞችን ማርባት ጀመሩ። ወደ ሥራ ገብተው መሥራት ከጀመሩ አሁን 20 ዓመት ሆኗቸዋል። በእነዚህ ዓመታት ግን ሥራቸው አልጋ ባልጋ ሆኖላቸው አይደለም ሲሰሩ የቆዩት።

ሌሎች አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንዳሉ ሆነው ብዙ ጊዚያት የሚያረቧቸው ላሞች እየሞቱባቸው ልባቸው ቢሰበርም፤ እንደምንም ተጣጥረው ሌሎች ላሞችን በመግዛት ላሞቻቸውን ያሳጣቸውን ሞት መልሰው ይበቀሉታል።

“በቀደም የሚታለቡ ሁለት ከብቶች ምን እንደነካቸው አላውቅም በተከታታይ ነበር የሞቱብኝ። እነዛ ሲሞቱብኝ በእልህ ሶስት ጥጃዎች ገዛሁ። ከዛ በኋላ እንግዲህ እስካሁን የሞተብኝ የለም። ነገር ግን በየጊዜው ላሞች የሚሞቱበት ሁኔታ ይገጥመኛል።” ይላሉ።

ወይዘሮ ወይንሸት ሁለት ጥጆችን ጨምሮ ዘጠኝ የፈረንጅ ላሞች ያሏቸው ሲሆን፤ ወንድ ጥጃ ካልሆነ ብዙ ጊዜ ከብት የመሸጥ ልምድ የላቸውም። ወንድ ጥጃ ሲሆን ከመኖ አቅርቦት አንጻር ስለሚቸገሩ ገና በተወለዱ በጥቂት ጊዚያት ውስጥ ገበያ አውጥተው እንደሚሸጡ ይናገራሉ።



ፎቶ፡ ገበየ ገብሬ

ወይዘሮ ወይንሸት ጥላሁን

“እኔ ላሞችን ሸጬ አላውቅም ከወንዶች በስተቀር፤ ለዛም ነው በርከት ሊሉ የቻሉት። አሁን ግን መኗቸውም እየተወደደ ስለሆነ መሸጤ አይቀርም። ጊዜው ለመሥራት ትንሽ ያስቸግራል፤ በመኖ አቅርቦት መንግሥት ቢያግዘን ጥሩ ነው።” ሲሉ ይገልጻሉ።

“ጥናት ተሰርቶ የከብቶች መኖ በመንግሥት በኩል የሚቀርብበት መንገድ ቢመቻች መልካም ነው። አሁን ከግለሰብ ስንገዛ በጣም ነው የሚወደድብን እስከ 60 ሺህ ብር የማይበቃበት ጊዜ አለ። ይህም የሚገኘው ገቢ ለላሞች መኖ ብቻ እንዲውል እያደረገሁ ነው።” ይላሉ።

አሁን ላይ ሁለት ላሞች የሚታለቡ ሲሆን፤ ሌሎቹ ነፍሰ ጡር ናቸው። እነዚህ ላሞች በቀን እስከ አስር ሊትር ድረስ ይታለባሉ። ዝርያቸው የተሻሻለ ላሞች ቢሆንም፤ አንደኛ የሚባሉ አይደለም በማለት ይገልጻሉ።

“ወደ ተለያዩ ቦታዎች ሄጄ እንዳየሁት እና ከወሰድኩት ከሥልጠና እንደተገነዘብኩት ከሆነ ላሞቹ ደረጃ አላቸው። እኔ የማረባቸው አንደኛ የፈረንጅ ላሞች አይመስሉኝም። ምክንያቱም እስከ 20 ሊትር ድረስ የሚታለቡ ላሞች እንዳሉም እንሰማለን። እና የእነዚህ ደረጃ ትንሽ የሚያንስ ይመስለኛል።” ይላሉ።

“በሥልጠናው ተነግሮኝ ከፍተኛ የወተት ምርት የሚያስገኙ ላሞችን ዝርያ ለያዙ ዶክተሮች ደውለን እንዲመጡ ስንነግራቸው እንደሚመጡ ቢገልጹልንም አይመጡም። አንዳንዴ ደግሞ ወረዳችን አይደለም የሚሉበትም ጊዜ አለ።” ሲሉ ይናገራሉ።

ላሞቹ ጽንስ ሊይዙባት የሚችሉት 24 ሰዓት ያለች ቢሆንም በቀኑ እኩሌታ ነው ዘረመሉ የሚሰጣቸው። ሰዓቱ ከዛ ካለፈ ወይም ካነሰ ዋጋ የለውም። ወይዘሮ ወይንሸት ምንም እንኳን ትምህርት ባይማሩም፤ ረጅም ዓመት በሥራው ላይ ከመቆየታቸው የተነሳ ላሞቻቸው በየትኛው ሰዓት ዝርያውን መወጋት እንዳለባቸው በራሳቸው ቆጥረው ነው የሚደርሱት።

ከብቶችን ማብላቱም ማጠጣቱም ትእግስት ይጠይቃል:: ምክንያቱም ወንፊት ላይ እህል ሲቀመጥ ነው ወደታች የሚወርደው:: ልክ እንደዛው ላሞቹም በሥርዓት ካልበሉ ካልጠጡ ደግሞ ምንም ዓይነት ጥቅም ማግኘት ከባድ ነው

ወደ ሥራው ከመግባታቸው በፊት ምንም ዓይነት እውቀቱ እንዳልነበራቸው የሚገልጹት ወይዘሮዋ፤ ወደ ሥራው ስገባ ምንም እውቀት አልነበረኝም። ነገር ግን ሰዎችን እየጠየኩ እና ወደ ሥራው ከገባሁ በኋላ ደግሞ አንዳንዴ በሚሰጠን ሥልጠና ነው እዚህ ልደርስ የቻልኩት ይላሉ።

“እኛ ላሞቹን የምናልባቸው በቀን ሶስት ጊዜ ነው። በሚሰጠን ሥልጠና ሶስት ጊዜ ማለብ አይፈቀድም ይሉናል። ግን ላሞቹ ስለለመዱ ካልታለቡ ይረብሹናል። ስለዚህ የግድ ሶስቴ መታለብ አለባቸው።” ሲሉ ይናገራሉ።

ወይዘሮ ወይንሸት ከከብቶቹ የሚያገኙትን ወተት ሸጠው ነው የላሞቹን መኖ የሚገዙትም ሆነ፤ ቤተሰቡን የሚያስተዳድሩት። ወተቱን የሚያስረክቡት ለካፌዎች ሲሆን፤ አንድ ሊትር በ70 ብር ነው የሚሸጡት።

የሚያገኙትን ወተት በራሳቸው ሱቅ ለማቅረብ አስበው ቢንቀሳቀሱ ከቤት ኪራይ ውድነት የተነሳ አልቻሉም። የሱቁ ጉዳይ ባይሳካላቸውም የገበያ ግንባር አላጡም። በጾም ወቅት ካልሆነ የገበያ ችግር የሌለባቸው ሲሆን፤ ለካፌዎች ወስዶ ከማስረከብ በተጨማሪ፤ የሰፈር ሰውም የሳቸውን ወተት ፈልጎ ነው የሚገዛላቸው።

“ከሚወጣው ወጪ አንጻር ወተቱ የሚሸጥበት ዋጋ አትራፊ አይደለም። ከብቶች ዘጠኝ እንደመሆናቸው እና የሚታለቡት ሁለቱ ብቻ በመሆናቸው ወጪው አይመጣጠንም። ያው ልጆቼ ጥሩ ቦታ ላይ ስላሉ እነሱም ይረዱኛል። እነሱ የሚሰጡኝን ገንዘብ ጨምሬ መኖ እገዛላቸዋለሁ።” ይላሉ።

አሁን ካሏቸው ዘጠኝ ከብቶች አምስቱ የሚታለቡ ሲሆኑ፤ የተቀሩት ጥጃ እና ጊደር ናቸው። ከሚታለቡ ላሞች ለጊዜው ወተት እየሰጡ ያሉት ሁለቱ ሲሆኑ፤ ሁለቱ ነፍሰጡር መሆናቸውን ያስረዳሉ።

ለጥጆቹ ወተት የሚሰጠው ታልቦ በእቃ ነው። “ጥጆቹ ይጥቡ ከተባለ መመለስ ከባድ ነው። የሚመልሳቸው ሰው የለም። ከዚህ በፊት እያስጠባሁ ለማለብ ሞክሬ ነበር ግን ትግል ነው። ላሞቹ እንዳያዩ ገና እንደወለዱ ነው በጨርቅ ሸፍኜ የማነሳቸው።” በማለት ይናገራሉ።

“በዚህ ሥራ የሚረዱኝ ልጆቼ እና ባለቤቴ ናቸው። ልጆቼ ሥራ ይዘው ትዳር መስርተው ስለወጡ ነው እንጂ በጣም ጎበዝ ናቸው። እነሱ ስለሚረዱኝ ሠራተኛ እንኳን አልፈልግም ነበር። አሁን ላይ አቅሜም እየደከመ ስለሆነ ሠራተኛ ለመቅጥር አስባለሁ። አሁን የሚረዱኝ ባለቤቴ እና አንድ ልጄ ከእኔ ጋር ስለሆነች እሷ ናት።” ይላሉ።

“ይህን ሥራ በመሥራቴ ባንክ ያስቀመጥኩት ገንዘብ ወይም ያፈራሁት ትልቅ ሀብት ባይኖረኝም፤ ቤቴን ለማሳደስ ችያለሁ። ሌላው ቤቴ ውስጥ የሚያስፈልጉኝን ነገሮች እንድሸፍን ከማድረግም ያለፈ ለማህበራዊ ወጪ የሚያስፈልጉኝን ወጪዎች እንድሸፍን ረድቶኛል። ልጆቼንም የማስቸግር ሰው አይደለሁም ግን የእናትነት ጉዳይ ስላለ ግዴታ ነው።” በማለት ይገልጻሉ።

ሁሉም ነገር ትእግስት ያስፈልገዋል የሚሉት ወይዘሮዋ፤ ከብቶችን ማብላቱም ማጠጣቱም ትእግስት ይጠይቃል። ምክንያቱም ወንፊት ላይ እህል ሲቀመጥ ነው ወደታች የሚወርደው። ልክ እንደዛው ላሞቹም በሥርዓት ካልበሉ ካልጠጡ ደግሞ ምንም ዓይነት ጥቅም ማግኘት ከባድ ነው ይላሉ።

ወይዘሮ ወይንሸት እስካሁን በሰሯቸው ሥራዎች የተለያዩ እውቅናዎችን እና ሽልማቶችም አግኝተዋል። ለልምድ ልውውጥ የተለያዩ አካባቢዎች ሄዶ የማየት እድሉም ገጥሟቸዋል።

“እውነት ለመናገር በዚህ ሥራ ዓለም ነው ያየሁበት፤ እናም ልጄ እየጦረኝ ነው የምለው። በከተማ ግብርና ውጤት በማምጣት ታጭቼ ዋንጫ፣ ሜዳሊያ ከመሸለም በተጨማሪ የብር፣ የልብስ ሽልማት ተሸልሜያለሁ። እሱ ብቻ ሳይሆን አዳማ እና ሌሎች አካባቢዎች ሄጄ በዘርፉ የሚሠሩ ሥራዎችን ጎብኝቼለሁ። ከወረዳም ሰዎች በየጊዜው እየመጡ ጎብኝተው ሃሳብ ይሰጡኛል።” ይላሉ።

“ላሞቹ የሚያድሩበትን ቦታ እንዳስፋፋ የፈቀዱልኝም የወረዳ ሰዎች ናቸው። በፊት ከብቶቹ በሚያድሩበት ቦታ ላይ ከላይ ቆጥ ሰርቼ ነው ሳር ሳስቀምጥ የነበረው። መጥተው ጎብኝተው የከብቶቹን መጎዳት ሲመለከቱ፤ አስፋፍቼ እንድሠራ ፈቀዱልኝ። አሁን ለሁሉቱም የተለያየ ቦታ ለማዘጋጀት ችያለሁ።” ሲሉ ይናገራሉ።

ከተማ ስለተወለዱ ብቻ መንቀባረር የለም የሚሉት ወይዘሮዋ፤ ከችግር ለመውጣት የማልፈነቅለው ድንጋይ የለም። ከብቶች ሳይኖሩኝ በፊት ልጆቼን ለማስተማር በተወሰነም ቢሆን እንዲረዳኝ በጎች አረባ ነበር። እነዚህን ሥራዎች ሲጀምሩ ምንም እውቀቱ እንዳልነበራቸው ይገልጻሉ።

“የመጀመሪያዋን ከብት ስገዛ ማለብ እንኳን ባለመቻሌ ባለቤቴ ነበር የሚያልበው። ከዛም ልጆቼን ከብት ማለብ አስተማራቸው። እኔም ቀስ በቀስ እየለመድኩ መጣሁ። አሁን እድሜ እየገፋ እየደከምኩ መጣሁ እንጂ ከተሠራ ለውጥ የማይመጣበት ምንም ምክንያት የለም።” ይላሉ።

ወተት የማለቡንም ሆነ የመናጡን ሥራ የሚሠሩት በባሕላዊ መንገድ ነው። ዘመናዊ መናጫ እና ማለቢያ ለመግዛት ገንዘብ እንደሚያስፈልጋቸው ለወረዳ አስረድተው ከባንክ ጋር እንደሚያስተሳስሯቸው ቃል የተገባላቸው ቢሆንም የመዘግየት ነገር እንዳለ ጠቁመዋል።

በመጨረሻም በጉለሌ ክፍል ከተማ ወረዳ አንድ ስለተደረገላቸው ድጋፍ ምስጋናቸውን የሚያቀርቡት ወይዘሮ ወይንሸት፤ በተጨማሪም ባለቤታቸውን እና ልጃቸውን አመስግነዋል።

ማረፊያ | አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ዛሬ ላይ ሆነን እነ እገሌ ዲግሪያቸውን ሊቀበሉ ነው የሚል ዜና ብንሰማ ውሃ የማያነሳና ለጆሮ የሚጎረብጥ ከመሆኑም በላይ እንደ እብደትም እንቆጥረው ይሆናል። ይህ ግን በአንድ ወቅት ትልቅ ዜና፤ ግዙፍ ርዕሰ ጉዳይም ነበር። ዛሬም በድሮው የሀገራችን የዘመን ምዕራፎች ውስጥ ስንሰነብት፤ በዋናነትም ሀገራዊና አህጉራዊ ሁነቶችና ታሪካዊ የሆኑ ጉዳዮችን እናገኛለን። ከእነዚህም ዲግሪ ሊቀበሉ ነው፤ የ46 ሚሊዮን ብሩ የኢትዮጵያ መርከብ፤ ኮንትሮባንዲስቷ አህያን ጨምሮ በአህጉራዊ ጉዳዮች ደግሞ፤ ለአፍሪካ ህብረት ምስረታ መሠረት በሆነው የአፍሪካ የነጻ መንግሥታት ጉባኤ፤ ግርማዊነታቸው ጋዜጠኞቹን አስደሰቱ፤ እነዚህና ሌሎችም በርከት ያሉ ርዕሰ ጉዳዮችን በማካተት ትውስታ አቅርበናል።

ዲግሪ ሊቀበሉ ነው

ሦስት ኢትዮጵያውያን መምህራኖች ለመጀመሪያ ጊዜ በአማርኛ ትምህርት በዚህ ዓመት መጨረሻ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የቢ ኤ ዲግሪ ሊቀበሉ የተዘጋጁ መሆናቸውን የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የትምህርት ክፍል ዳይሬክተር፤ ዶክተር አክሊሉ ሀብቴ በሰጡት ወሬ ገልጸዋል።

የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ዋነኛ ቋንቋ በሆነው በአማርኛ ትምህርት፤ የቢ ኤ ዲግሪያቸውን ለመቀበል የታደሉት የመጀመሪያዎቹ ኢትዮጵያውያንም፤ አቶ አምደ ሥላሴ ጀምበሬ፤ አቶ ክንፉ ዱሬሣ፤ አቶ ደምሴ ማን አህሎት የተባሉት በኮሌጅ አራተኛ ክፍል የመምህርነት ትምህርት የሚከታተሉ ወጣቶች ናቸው።

(አዲስ ዘመን ሰኔ 12 ቀን 1952ዓ.ም)

46 ሚሲዮን ብር የተገዛው መርከብ ሥራ ጀመረ

ምፅዋ፤(ኢ.ዜ.አ) ኢሠፓና አብዮታዊው መንግሥት የኢትዮጵያን የውጭ ንግድና የባህር ትራንስፖርት አገልግሎት ለማስፋፋትና ለማጠናከር በቀየሱት መርሐግብር መሠረት በ46 ሚሊዮን ብር የተገዛው አንድ ዘመናዊ የንግድ መርከብ ትናንት ተመርቆ አገልግሎት መስጠት ጀመረ።

“አንድነት” የተባለውና ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ ፈረስ ጉልበት ያለው ይኸው ዘመናዊ መርከብ የናቪጌሽንና ሌሎችም መሣሪያዎች፤ 4 ባለ 12.5፤ 2 ባለ 20 እና 1 ባለ 5 ቶንስ የመጫኛና የማራገፊያ ክሬኖች ያሉት ሲሆን 10ሺህ 886 ቶንስ እቃ ለመጫን የሚችል መሆኑ ታውቋል።

(አዲስ ዘመን ሰኔ 23 ቀን 1979ዓ.ም)

አህያ የኮንትሮባንድ እቃ ጭና ተያዘች

ባለቤትነቷ የማን እንደሆነ ያልታወቀች አንዲት አህያ፤ ግምቱ አንድ ሺ አምስት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር የሆነ የኮንትሮባንድ ዕቃ ተጭና ጨረቲ ከተባለው ቀበሌ በፊናንስ ፖሊሶች ተያዘች።

ኮንትሮባንዲስቷ አህያ ፤ ማንነቷን ለማጣራት ተይዛ የጫነችው እቃ በተመረመረ ጊዜ፤ ቀረጥ ያልተከፈለበት አሥራ ሦስት ጣቃ ናይሎን ጨርቅና ዘጠና ስምንት እስቴካ ሮዝማንስ ሲጋራ ይዛ መገኘቷን የከሚሴ የፊናንስ ፖሊስ አዛዥ ሻምበል ሰብሉ ክብረት ገልጠዋል።

ወዲያው አህያዋ ቀረጥ ካልተከፈለበት ጭነቷ ጋር ይፋትና ጥሙጋ አውራጃ ፍርድ ቤት ቀርባ፤ ከነጭነቷ ለመንግስት በውርስ ስም ገቢ የተደረገች መሆኗን የፍርድ ቤቱ ዓቃቤ ሕግ አቶ አበበ ኦዳ ገልጠዋል።

(አዲስ ዘመን ነሀሴ 12 ቀን 1962 ዓ.ም)

ሁለተኛው የአፍሪካ ነጻ መንግሥታት ጉባኤ ከ9 ቀን ስብሰባ በኋላ መፈጸም

አሥራ ሁለት ቀኖች ያህል የግልና የይፋ ስብሰባ በማድረግ ላይ ሰንብቶ የነበረው፤ ሁለተኛው የአፍሪካ ነፃ መንግሥታት ጉባኤ የሥራ ውጤት በሦስት ምድብ አማካይነት ከሰማና በእያንዳንዱ ድምፅ አንቀጽ ከሰጠ በኋላ በከቡር ፕሬዝዳንቱ አማካይነት ሰኔ 18 ቀን 1952ዓ.ም ተዘግቶአል።

(አዲስ ዘመን ሰኔ 19 ቀን 1952ዓ.ም)

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከየሀገሩ ስመጡ ጋዜጠኞች ፕሬስ ኮንፈረንስ ስለማድረጋቸው

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤ መልካም ፈቃዳቸው ሆኖ ሰኔ 17 ቀን 1952ዓ.ም ከእኩለ ቀን በላይ 10 ሰዓት ተኩል በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥታቸው ላይ ተገኝተው አዲስ አበባ ላይ በተከፈተው የአፍሪካ ነጻ መንግሥታት ጉባኤ ላይ የጉባኤውን ሁኔታ ለመመልከት ከየሀገሩ የመጡትን 38 ጋዜጠኞችን ተቀብለው ፕሬስ ኮንፈረንስ አድርገውላቸዋል።

በዚህም ጊዜ እያንዳንዱ ጋዜጠኛ እየተነሳ ስለ አፍሪካ ነጻ መንግሥታት ጉባኤና በጠቅላላው አፍሪካን ስለሚመለከቱ ጉዳዮች ግርማዊነታቸው ያላቸውን አስተያየት እንዲገልጹላቸው ላቀረቡላቸው ጥያቄ አጥጋቢ የሆነ መልስ በመስጠት አስደስተዋቸዋል።

(አዲስ ዘመን ሰኔ 18 ቀን 1952ዓ.ም)

አዲስ ከተማ መቆርቆር

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለሕዝባቸው የኑሮ መሻሻልና ለሀገራቸው ልማት ባቀዱት የአምስት ዓመት ፕላን መሠረት በጎጃም ጠቅላይ ግዛት ባሕርዳር ላይ አንድ ከተማ እንዲሠራ ትእዛዝ ሰጥተው የከተማው ፕላን ተሠርቶ ለከተማው ውበትና በከተማው ውስጥ ለሚኖረው ሕዝብ ምቾት የሚያስፈልጉት ልዩ ልዩ የዘመናዊ ከተሞች ዕቅዶች በመጠናትና በመሠራትም ላይ ይገኛሉ።

(አዲስ ዘመን ታህሳስ 23 ቀን 1952ዓ.ም)

መገናኛዎች

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፤ የሕዝባቸውን ችግር ማስወገድ የዘወትር ተግባራቸው በመሆኑ በሸዋና በጎጃም ጠቅላይ ግዛቶች ካንዱ ወዳንዱ የሚሔደው ሕዝባቸው ታላቁን የዓባይ ወንዝን በሚሻገርበት ጊዜ በውሀው ኃይልና በውሀው ውስጥ በሚገኙት አዞዎች በሚደርስበት አደጋ የገጠመውን ጉዳት በመመልከት፤ በታላቁ የዓባይ ወንዝ ላይ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የፈጀ ታላቅ የሆነ ዘመናዊ ድልድይ አሠሩለት።

....

እንዲሁም ደግሞ በጎጃም ጠቅላይ ግዛት አዲስ በሚሠራው ባሕር ዳር ከተማ ውስጥ አንድ ኤንተርናሽናል የሆነ ታላቅ ዘመናዊ የአውሮፕላን ማረፊያ እንዲሠሩ ታቅዶ ከግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ጥናቱ በሚያስቸኩል በመራመድ ላይ ይገኛል።

(አዲስ ዘመን ታህሳስ 23 ቀን 1952ዓ.ም)

ዓለም አቀፍ

ወታደራዊ ሕግ ለመደንገግ የሞከሩት ፕሬዚዳንት ከሀገሪቱ እንዳይወጡ ታገዱ

ወታደራዊ ሕግ ለመደንገግ በመሞከር ምርመራ እየተደረገባቸው የሚገኙት የደቡብ ኮሪያ ፕሬዚዳንት ዩን ሱክ ዮል ከሀገር እንዳይወጡ ዕገዳ ተጣለባቸው። የደቡብ ኮሪያ አመራሮች ፕሬዚዳንቱ ከሀገሪቱ እንዳይወጡ የጉዞ ዕቀባ መጣላቸውን አስታውቀዋል።ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ ክስ ሊመሠርትባቸው ከጫፍ ደርሶ ነበር። ሆኖም ግን የገዢው ፓርቲ (ፒፒፒ) አባላት የሆኑ የሀገሪቱ ምክር ቤት አባላት ፕሬዚዳንቱ እንዲከሰሱ የተሰጠውን ድምጽ አግደዋል።

ፕሬዚዳንቱ የሥልጣን ዘመናቸውን ለማገድ እና በውጭ እንዲሁም በሀገር ውስጥ ጉዳዮች ጣልቃ ላለመግባት መስማማታቸውን ተከትሎ ነው እንዳይከሰሱ የተወሰነው። ተቃዋሚ ፓርቲው ‘ዴሞክራቲክ ፓርቲ’ ግን ክስ ሳይመሠረት መቅረቱን አልተቀበለውም።የፓርቲው መሪ ፓርክ ቻን-ዴ “ይህ ሕገ ወጥ፣ ሕገ መንግሥቱን የሚጻረር እና ሁለተኛ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ነው” ሲሉ ተናግረዋል።

ለአጭር ጊዜ የቆየው ወታደራዊ ሕግ መደንገጉን ተከትሎ በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ለተቃውሞ አደባባይ ወጥተዋል።ፕሬዚዳንቱ ከሥልጣን እንዲወገዱ እና እንዲከሰሱ ጠይቀዋል። ፕሬዚዳንቱ ባይከሰሱም ከወታደራዊ ሕጉ መደንገግ ጋር በተያያዘ ተሳትፎ ያላቸው ቁልፍ የሀገሪቱ ባለሥልጣናት እርምጃ ተወስዶባቸዋል።

ወታደራዊ ሕግ እንዲደነገግ ለፕሬዚዳንቱ ሃሳብ ያቀረቡት የቀድሞው መከላከያ ሚኒስትር ኪም ዮንግ-ሁን ትናንት በቁጥጥር ሥር ውለዋል። ያለፈው ሳምንት ረቡዕ ሥልጣናቸውን ለቀው “ኃላፊነት እወስዳለሁ” ብለው ነበር። የመከላከያው ስለላ ክፍል ኮማንደር ይዎ ኢን-ሁንግ እና ኤታማዦር ሹሙ ፓርክ አን-ሱ ላይ የጉዞ ማዕቀብ ተጥሏል።

ሥልጣናቸውን ለቀው “የሕዝቡ እና የፕሬዚዳንቱን ፍላጎት ባለማስጠበቄ ኃላፊነት እወስዳለሁ” ያሉት የቀድሞው የሀገር ውስጥ ሚኒስትር ሊ ሳንግ-ሚንም የጉዞ ዕቀባ ተጥሎባቸዋል። የገዢው ፓርቲ ፒፒፒ መሪ ሀን ዶንግ-ሁን፣ ፕሬዚዳንቱ በሀገር ውስጥ እና በውጭ ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገቡ እንዲሁም ጠቅላይ ሚኒስትር ሀን ደክ-ሱ ኃላፊነት እንደሚረከቡ ተናግረዋል።

“ፕሬዚዳንቱ ሥልጣን ሳይለቅ በፊት ዲፕሎማሲን ጨምሮ በማንኛውም ጉዳይ ጣልቃ አይገባም” ብለዋል። የተቃዋሚ ፓርቲው ‘ዴሞክራቲክ ፓርቲ’ መሪ ፓርክ ቻን-ዴ ግን “ሁለተኛ መፈንቅለ መንግሥት” ሲሉ ነው ክስተቱን የገለጹት። የፓርቲው ተወካይ ኪም ሚን-ሱክም የገዢው ፓርቲ መሪ ውሳኔ ለማሳለፍ “ሥልጣን የለውም” ሲሉ ተችተዋል።

“ጠቅላይ ሚኒስትሩ እና የገዢው ፓርቲ ማንም ሥልጣን ሳይሰጣቸው የፕሬዚዳንቱን ኃላፊነት መረከባቸው ሕገ መንግሥቱን ይጻረራል” ብለዋል።ፕሬዚዳንቱ ለሀገሪቱ ብሔራዊ መከላከያ ትዕዛዝ የማስተላለፍ ሥልጣናቸው ባለበት እንደሚቆይ ተገልጿል። ይህ ማለት ከሰሜን ኮሪያ ትንኮሳ ቢኖር የመጨረሻውን ውሳኔ የሚሰጡት ፕሬዚዳንቱ ይሆናሉ ማለት ነው። በሚዮንግጂ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር ሺን ዩል ለኮሪያ ሄራልድ እንዳሉት፣ ፕሬዚዳንቱ “ሃሳባቸውን ከለወጡ ወደ መሪነት መመለስ” ይችላሉ።

“ማንም ሊያስቆማቸው አይችልም” ሲሉ አስረድተዋል።ፕሬዚዳንቱ ወታደራዊ ሕግ በመደንገጋቸውና ሕዝቡ ላይ በፈጠረው “ጭንቀትና ውጣ ውረድ” በይፋ ዜጎችን ይቅርታ ጠይቀው በድጋሚ ወታደራዊ ሕግ እንደማይደነግጉ አስታውቀዋል።ተቃዋሚዎች ግን ፕሬዚዳንቱ እንዲከሰሱ ግፊት ማድረግ እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል።”ለመጪው የገና በዓል እና ለአዲስ ዓመት ስጦታችን ሀገራችንን ወደነበረችበት መመለስ ነው። የተቃዋሚ ፓርቲ መሪው ፕሬዚዳንቱ የደቡብ ኮሪያን ምጣኔ ሀብት በማዳከሙ ሥልጣን ሊለቅ ይገባል” ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ወታደራዊ ሕግ (ማርሻል ሎው) የሲቪል ባለሥልጣናት ሥራቸውን በአግባቡ ማከናወን እንደማይችሉ በሚቆጠርበት ጊዜ ወታደራዊ ባለሥልጣናት እንዲመሩ የሚደረግበት ጊዜያዊ አገዛዝ ነው። አንዲት ሀገር በወታደራዊ ሕግ ስር በምትሆንበት ወቅት የሲቪል መብቶች መታደግ እንዲሁም ወታደራዊ ሕጉ ሊራዘም የሚችልበት ሁኔታ ይፈጠራል። በደቡብ ኮሪያ ለመጨረሻ ጊዜ ወታደራዊ ሕግ የታወጀው በአውሮፓውያኑ 1979 ሲሆን፤ ወቅቱም ሀገሪቱን ለበርካታ ዘመናት የገዙት አምባገነኑ ፖርክ ቹንግ ሂ በመፈንቅለ መንግሥት መገደላቸውን ተከትሎ ነው።

ስፖርት



የእጅ ኳስ ፕሪሚየር ሊግ በሦስት ዙር ይካሄዳል

ዓለማየሁ ግዛው

የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ስፖርት ፕሪሚየር ሊግ መካሄድ ከጀመረ ዘንድሮ ዘጠናኛ ዓመቱን አስቆጥሯል። በፕሪሚየር ሊጉ አስር ክለቦች በተመረጡ ከተሞች ውድድራቸውን የሚያከናውኑ ሲሆን፣ ክለቦች ካለባቸው የፋይናንስ እጥረት አኳያ እንዲሁም ለስፖርቱ እድገት ሲባል ክለቦቹ የሚኙበትና ስፖርቱ በስፋት በሚዘወተርበት አካባቢ መካሄድ እንደሚኖርበት ሃሳብ አቅርበዋል።

የ2017 ዓ.ም የኢትዮጵያ እጅ ኳስ ወንዶች ፕሪሚየር ሊግ ውድድር ከታኅሳስ 6/2017 ዓ.ም ጀምሮ በሃዋሳ ከተማ በአስር ክለቦች መካከል ለማካሄድ የእጣ ማውጣት ስነ-ስርዓት ኅዳር 28/2017 ዓ.ም የክለብ ኃላፊዎች፣ ተወካዮች እና አሰልጣኞች በተገኙበት ተከናውኗል። ፌዴሬሽኑ የዓመቱን ውድድር ሃዋሳን ጨምሮ በሶስት ከተሞች (ሃዋሳ፣ ድሬዳዋና አዲስ አበባ) አካሂዶ ለማጠናቀቅ ሃሳብ ያቀረብ ቢሆንም፣ ለውድድሩ ከተመረጡት ከተሞች አኳያ ከክለቦች ቅሬታ ቀርቦበታል። የውድድሩን ከተሞችን ስፖርት መሰረተ ልማትን፣ ጸጥታን፣ ትራንስፖርት ምቹነትንና አገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን መሰረት በማድረግ በሶስቱ ከተሞች የአንደኛና የሁለተኛ ዙር ግጥሚያዎችን ለማካሄድ ማቀዱን ፌዴሬሽኑ አስታውቋል።

አዲስ አበባ ከተማ ላይ ሁለት ውድድሮችን ለማካሄድ የታቀደ ሲሆን የመጀመሪያ ዙር አንድ ውድድርና የመዝጊያ ውድድር እንደሆነም ተነግሯል። ሃዋሳና ድሬዳዋ ከተሞች ውድድሩን ለማስተናገድ በሚደረገው ጥረት ከአመራሮች ጋር ውይይት መደረጉ የተገለጸ ሲሆን ቅድመ ዝግጅቶች እየተካሄዱም ይገኛሉ።

ፌዴሬሽኑ በቦርድና በስራ አስፈጻሚ ደረጃ ተወያይቶ ውድድሩ የሚካሄድበት ጊዜና የሚያስተናግዱ ከተሞችን ይፋ ቢያደርግም፣ ክለቦች ከእጣ- ማውጣትና የውድድር ከተሞችን ከማሳወቅ አስቀድሞ እነሱን ባሳተፈ መልኩ ውይይትና ግምገማ መደረግ ነበረበት በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል። የ2016 ዓ.ም ውድድር ሳይገመገም እና ጥፋት ያጡፉ ዳኞችም

ፌዴሬሽኑ ስእያንዳንዱ ክለቦች ደረጃቸውን የጠበቁ ሶስት ሶስት ኳሶች አበርክቷል፣

ሆኑ ክለቦች ተገቢውን ውሳኔ ሳያገኙ ወደ ውድድር መገባቱ ትክክል እንዳልሆነም ጠቁመዋል። የክለብ ተወካዮችና አሰልጣኞች ከውድድሩ አካሄድ፣ ከዳኝነት ስርዓት፣ ከበጀት እና ሌሎች ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ጥያቄዎችን አንስተው ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል። በዚህም መሰረት የውድድር ጊዜው ካለው የበጀት እጥረት እና የትራንስፖርት መወደድ አኳያ ወደ ሶስት ጊዜ እንዲያጥር የሚል አስተያየትም ተነስቷል።

በተለይ የፀጥታ ስጋት ያለባቸው አካባቢዎች የአየር ትራንስፖርት ተጠቅመው የሚመጡ ክለቦች ትኩረት ካልተሰጣቸው በበጀት እጥረት ምክንያት የመፍረስ እጣ ፈንታ እንደተጋረጠባቸውም ተመላክቷል። በተጨማሪም ውድድሩ በትላልቅ ከተሞች መካሄዱ ክለቦች ለቀን አበል የሚሰጣቸው ወጪና የሚያወጡት የማይመጣጠን እንደሆነም ገልጸዋል።

ውድድሩ ሁሌም ከዓመት ዓመት በተመሳሳይ ከተሞች እየተካሄደ ቢሆንም በስፖርቱና ክለቦች ላይ ለውጥ ማምጣት ባለመቻሉ ክለቦች የሚገኙባቸውና ስፖርቱ በስፋት የሚዘወተርባቸው አካባቢዎች መካሄድ እንደሚኖርበትም ክለቦች አሳስበዋል። ውድድሩን የሚመሩት ዳኞች ቁጥር መቀነስና መደጋገም ከስፖርተኛው ጋር መላመድ መናናቅ እየፈጠረ በመሆኑ በትኩረት መሰራት እንደሚኖርበት ክለቦች አሳስበዋል። የውድድር መረሃ ግብር መጣበብ ስፖርተኛውን ለጉዳት እንዳይዳርግና ፉክክሩ እንዳይቀንስም ስጋታቸውን ገልጸዋል።

የፌዴሬሽኑ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ሰጠኝ አዲስ፣ ውድድሩ የእጅ ኳስ ክለቦች የማይገኙባቸው አካባቢዎች የሚካሄደው ከተሞቹ ክለብ እንዲይዙ ለማነቃቃትና ስፖርቱን ለማሳደግ መሆኑን ተናግረዋል። ውድድሩን ከስህተትና ከዲሲፕሊን ግድፈት በጸዳ መልኩ ለማካሄድ ዝግጅት ተጠናቋል። ከሃዋሳ ውጭ የውድድር ስፍራዎቹን ለመወሰን በውድድር ደንቡ መሰረት መታየት እንደሚኖርበትም አመላክተዋል።

የፌዴሬሽኑ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሞላ ተፈራ በበኩላቸው፣ ክለቦች የሚያነሷቸው ጉዳዮች የሚጠቅሙና መማሪያ በመሆናቸው ፌዴሬሽኑ በቀጣይ የግምገማና የውይይት መድረክ እንደሚያዘጋጅ ገልጸዋል። በዚህም መሰረት ያለፈውን የውድድር ሂደት መገምገም ያልተቻለው በአህጉር አቀፍ ውድድሮች ምክንያት የጊዜ መጣበብ በመኖሩ መሆኑንና በቀጣይ የውይይትና ግምገማ መድረክ ለማዘጋጀት መታቀዱን እንዲሁም በዓለም አቀፍ ተሞክሮን መሰረት ሰነድ እየተዘጋጀ እንደሆነ ጠቁመዋል። የዳኞችን ቁጥር መጨመርና ተገቢውን የሙያ ስልጠና ለመስጠት መታቀዱንም ጠቅሰዋል።

በውድድር መርዘም ምክንያት ወጪ እየበዛ ነው፣ የዳኝነት ችግር መኖር፣ የውድድር መቀነስ የስፖርተኛው አካል ብቃት ላይ ጫና ይፈጥራል የሚሉና የውድድር ከተሞች ተመሳሳይ መሆን ለስፖርቱ እድገት አልጠቀመም የሚሉ ነጥቦች በክለቦች ተነስቷል።

ውድድሩ በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በሁለት ዙሮች ተከፍሎ በሶስቱ ከተሞች እንደሚካሄድ ፌዴሬሽኑ በሰጠው ማብራሪያ ተጠቁሟል። በዚህም መሰረት የአንደኛ ዙር የፕሪሚየር ሊግ ውድድር አዲስ አበባ 25 እና ሃዋሳ ከተማ ላይ 20 በሁለቱ ከተሞች 45 ጨዋታዎችን አካሂዶ የመጀመሪያውን ዙር ውድድር ለማጠናቀቅ አቅዷል። በሁለተኛ ዙር የሊጉ ውድድር እንዲሁ በድሬዳዋ ከተማ ላይ 25 ጨዋታዎችና አዲስ አበባ ከተማ ላይ 20 ጨዋታዎችን አካሂዶ ለማጠናቀቅ እንደ ተወሰነም ተጠቅሷል። በሳምንት አምስት ጨዋታዎች የሚካሄዱ ሲሆን፤ ከአንደኛ እስከ አራተኛ ሳምንት ጨዋታዎች ከታህሳስ 6 እስከ 15/2017 ዓ.ም እና የአንደኛ ዙር ከአምስተኛ እስከ ዘጠነኛ ሳምንት በአዲስ አበባ ከተማ ከጥር 26 እስከ የካቲት 3/217 ዓ.ም ድረስ ይካሄዳል ተብሏል።

ባህር ዳር ከነማ፣ ፋሲል፣ መቐለ 70 እንደርታ፣ አሜድላ፣ ቂርቆስ፣ ኮልፌ፣ መቻል፣ ማረምያ፣ ሚዛን አማን እና ከምባታ ዱራሜ የሚሳተፉ ይሆናል።